
ዳግ ሂዋርድ ሚልስ

የታዋቂ መጽሐፎች "ሜጋ ቤተክርስቲያን" እና "የመጋቢነትህ አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ አሳድግ" ጸሐፊ



# የእረኝነት ጥበብ

የመጋቢነት አገልግሎት ርዕሶች

ካልተገለፀ በቀር፣ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. ከታተመው የአማርኛ መፅሐፍ ቅዱስ ነው።


Email Dag Heward-Mills:
bishop@daghewardmills.org
evangelist@daghewardmills.org

Find out more about Dag Heward-Mills at:
www. daghewardmills.org
www. lighthousechapel.org
www.healingjesuscrusade.org

Write to:
Dag Heward-Mills
P.o.Box 114
Korle-Bu
Accra
Ghana

ላይትሃውስ ቻፐል ኢንተርናሽናል
ስልክ +251912063821
መ.ሳ ቁጥር 15134
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ



ይህንን መፅሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያላሳታሚው ፈቃድ ማባዛት የተከለከ ለ ነው።

# ማውጫ

1. በጎች እንዲያርፉ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው?.................................... 1
2. በጎች ውሃ የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው? ........................................ 4
3. መፈንገል በበጎች ላይ የሚያመጣው ጉዳት ምንድነው? ................................ 6
4. በጎች መመራት የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው? ....................................... 10
5. በጎች የለመለመ መስክ የሚፈልጉት ለምንድነው?........................................ 13
6. በጎች በሸለቆዎች መካከል ማለፍ የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?......................... 15
7. አልጠግብ ባይ በጎች ምን ያጋጥማቸዋል?............................................. 18
8. በትር ለበጎች ምን ይጠቅማል?....................................................... 20
9. ምርኩዝ ለበጎች ያለው ጥቅም ምንድነው?............................................ 22
10. በጠላቶቻቸው ፊት ለፊት ገበታን ማግኘት ለበጎች ያለው ትርጉም ምንድነው?......... 24
11. በጎች በዘይት መቀባት ለምን ያስፈልጋቸዋል? ......................................... 27
12. የእረኛው ፅዋ የተረፈ መሆን ለበጎች ያለው ፋይዳ ምንድነው ? ......................... 31
13. በጎች በእረኛቸው ቤት መኖር የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው? ........................... 33
14. ያለ እረኛ መሆን ለበጎች ምን ትርጉም አለው? ......................................... 35
15. እረኞችንም የሚያጠቃ የበጎች በሽታ....................................................... 37
16. በጎች ለምን ይታመማሉ?........................................................... 41
17. የእረኛው ሦስት ግቦች.............................................................. 47
18. በበሩ ያልገቡትን በጎች እንዴት መለየት ይቻላል? ...................................... 48
19. የእረኝነት ተግባራት ................................................................ 58
20. የእረኝነት ተግባራት ................................................................ 60
21. እረኞች ለበጎች ሊተጉላቸው የሚገባቸው አምስት መንገዶች ............................ 61
22. ጠባቂው እረኛ ያህዌ ............................................................... 64
23. የእረኝነት ተግባራት ................................................................ 66
24. የእረኝነት ተግባራት ................................................................ 68

25. ደም መጣጭ የቤተክርስቲያን መጋቢዎች ........................................ 70
26. የያህዌ የእረኝነት ጥበብ ........................................ 75
27. መልካም እረኛ ለመሆን የሚረዱ ሠላሳ አምስት ቁልፍ ነገሮች ........................................ 79
28. ከበጎችህ ጋር ሊኖረህ የሚገባ የተለያዩ ዓይነት ግንኙነቶች ........................................ 93
29. የሞያተኛ እረኞች አሥራ ሁለት ባህሪያት ........................................ 105
30. ዘጠኝ የሞያተኛ መጋቢ አይነቶች ........................................ 112
31. ቅር የሚያሰኙ እረኞች ........................................ 119
32. የእረኞች ዕድገት ሃያ ሁለት ደረጃዎች ........................................ 127
33. መንፈሳዊ ልጅ ወደ እረኝነት የሚያድግበት መንገድ ........................................ 133
34. እረኛ ሊያደግባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ........................................ 138
35. አንድ ወጣት ወደ እረኝነት የሚደርሰው እንዴት ነው? ........................................ 145
36. ልብህ የአገልግሎትህ ማዕከል ነው ........................................ 151
37. ከሰው የተፈጥሮ ልብ ጋር በማወዳደር ስለመንፈሳዊ ልብ መረዳት ........................................ 154
38. የእረኞች ልብ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? ........................................ 157
39. ንጹህ ልብ ይኑርህ ........................................ 160
40. አልበገር ባይ ልብን አስወግድ ........................................ 163
41. ጤናማ ልብ ይኑርህ ........................................ 165
42. ከሀመምተኛ ልብ ተፈወስ ........................................ 168
43. የሚያበረታ ልብ ይኑርህ ........................................ 171
44. ከአሉታዊ ልብ ተጠንቀቅ ........................................ 174
45. አስተዋይ ልቦና ይኑርህ ........................................ 178
46. ግትር ልብን ተቃወም ........................................ 181
47. ባለ ተስፋ ልብ ይኑርህ ........................................ 183
48. አገልግሎትህን ማስፋት የምትችልበት መንገድ ........................................ 187
49. እረኛ ብርሃን ነው ........................................ 192
50. አንዳንድ ሰዎች ለምንድነው ትልቅ ብርሀን የሚሆኑት? ........................................ 195

51. ትልቅ ብርሀን ልትሆን የምትችልበት መንገድ ........................................ 197

52. የአገልግሎት መንፈሳዊ ጅማቶች ........................................ 199

53. የአገልግሎት እንቅፋቶች ........................................ 203

54. በክፉ ቀን የሚከሰትን መዘግየት ማሸነፍ ........................................ 206

55. መዘግየት በሚከሰትበት ጊዜ የሚነሱ አሥራ አምስት ክፉ ነገሮች ........................ 212

56. መዘግየት የሚከሰትባቸው ስምንት ምክንያቶች ........................................ 217

57. የእግዚአብሔር እርዳታ የሌለበት አገልግሎት ምን ይመስላል? ........................ 220

58. እግዚአብሔር ሲያሳድግህ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል? ........................ 223

መታሰቢያ

ለፓትሪክ እና ጆይ ብሩስ

በሰሜን ጋና ለተሰራው ትልቅ ሥራ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ትርጉም:- መስፍን ተስፋዬ
አርታኢ:- መጋቢ ምንሊክ ታምራት

# ክፍል አንድ

## በጎች

## ምዕራፍ 1

# በጎች እንዲያርፉ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው?

"ኑ፥ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ በእርሱ ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት እንበርከክ እርሱ አምላካችን ነውና፥እኛ የማሰማርያው ሕዝብ የእጁም በጎች ነንና።"

*መዝሙር 95፡6-7*

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ በጎች ተብለው ተጠርተዋል፡፡ ኢየሱስ "እረኛ እንደሌላቸው" በጎች መስሎናል፡፡ በጎችን በሚገባ ለማስማራት ሕይወታቸውንና ባህሪያቸውን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከመጋቢህ ጋር በሚኖርህ ግንኙነት ራስህን እንደ በግ ልትመለከት ይገባሃል፡፡ እንዲሁም የቤተክርስቲያንህን አባላት በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ትችል ዘንድ እንደ በጎች ልታያቸው ይገባሃል፡፡ ዳዊት በሃያ ሦስተኛው መዝሙር ከራሱ የእረኝነት ልምምድ በመነሳት ስለበጎች ሕይወት ይናገራል፡፡ ይህ ጉልህ "የበጎች ሕይወት" አገላለጽ የወጣው ራሱን እንደ እግዚአብሔር የግል በግ አድርጎ ከሚቆጥረው እና የእረኝነት ልምድ ካለው እስራኤላዊ እረኛ አፍ ነው፡፡

> "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።"

*መዝሙር 23፡1-6*

ፊሊፕ ኬለር በተባለው በብሪታኒያ ኮሎምቢያ ለስምንት ዓመት ያህል በጎችን ሲያረባ በነበረው የዚህ ዘመን እረኛ ስለ በጎች በገለጸው አገላለጽ ውስጥ ስለበጎች ሕይወት ዳዊት ከተናገረው ጋር የሚመሳሉ ነገሮችን በማግኘቴ በጣም አስደስቶኛል፡፡

እርሱ በዘመናዊ መልኩ የበጎች እረኝነትን በተግባር የተለማመደ ሰው ነው፤ በመዝሙር 23 ለሰፈሩት መገለጦች አስደናቂ ማፅናኛዎችን ሰጥቷል።

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።"

መዝሙር 23፡1-2

በጎች ለማረፍ እንዲሚላላቸው የሚፈልጉት ነገር አለ። በቤተክርስቲያንህ ያሉትን በጎች በለመለመ መስክ እንዲያድሩና ከአንተ ጋር እንዲቆዩ ማድረግ አለብህ። የፈሩ በጎችን ማረጋጋት፤ ሰዎችንም እንደ ቤተሰብ በዙሪያህ መጠበቅ ይገባሃል። ፊሊፕ ኬለር ከእረኝነት ልምዱ በመነሳት በጎች እንዲያርፉ የሚያደርጋቸውን ጥቂት ነገሮችን ይናገራል። የሚከተሉት አራት ነጥቦች እያንዳንዳቸው አንዳንድ ሰዎች ለምን በእግዚአብሔር ቤት መቆየት እንደማይችሉ የሚገልጹ ናቸው። በአባላት መካከል ያለ ውጥረት፣ ፍርሀት፣ የአጋንንት ጥቃት፣ እንዲሁም ከመድረክየመልካም ምግብ መታጣት እነኚህ ሁሉ በጎች በቤተክርስቲያን እንዳይቀመጡ የሚያደርጉ ምክንያቶች ናቸው። ፊሊፕ ኬለር እንደዚህ ይላል፤

1. በጎች የሚያርፉት ከፍርሀት ነጻ ሲሆኑ ነው፡- ድንጉጦች ስለሆኑ ፍጹም ከማንኛውም ፍርሃት ፍፁም ነጻ ካልሆኑ በስተቀር ለማረፍ ፈቃደኛ አይሆኑም። በጎች በጣም ድንጉጦችና በቀላሉ የሚረበሹ ናቸው፤ከጥሻ ውስጥ በድንገት ብቅ የምትል ጥንቸል መንጋውን ሁሉ ልታናውጥ ትችላለች። አንድ የደነበረ በግ ፈርቶ ከሮጠ በርካታ በጎች በጭፍን ፍርሀት እርሱን ተከትለው ይሮጣሉ እንጂ ምን እንዳስፈራቸው ለማወቅ እንኳ ጊዜ አይሰጡም።

2. በጎች በሠላም የሚተኙት ከሌሎች መሰል በጎች ጋር ቅራኔ ከሌላቸው ነው፡- ከመንጋው ማኅበራዊ ኑሮ የተነሳ በጎች ከመሰሎቻቸው ጋር ፍጹም ከግጭት ነጻ ካልሆኑ አርፈው አይተኙም።

3. በጎች በሠላም የሚተኙት በዝንቦችና ሌሎች ተባዮች ካልተሰቃዩ ነው፡- በጎች በዝንቦችና ሌሎች ተባዮች ከተበሉ አርፈው

አይተኙም። ዘና የሚሉት ከእነኚህ ተባዮች ነጻ የሆኑ እንደሆነ ብቻ ነው።

4. በጎች በሠላም የሚተኙት ያልተራቡ እንደሆነ ነው፡- በጎች መብላት እንዳለባቸው እስከተሰማቸው ድረስ አይተኙም። ከረሃብ ነጻ መሆን አለባቸው። ለማረፍ በአስተማማኝ ሁኔታ ከፍርሃት፣ ከጭንቀት፣ ከብስጭት እና ከረሀብ ነጻ መሆን ያስፈልጋል።

## ምዕራፍ 2

# በጎች ውሃ የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?

*"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛልበዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።"*

**መዝሙር 23፡1-2**

ቀደም ሲል የተመለከትነው ዘመናዊው እረኛ ፊሊፕ ኬለር ከበጎች ጋር የነበውን ልምድ መሠረት በማድረግ በጎች ጤናማ ሆነው ለመኖር ውሃ ምን ያህል እንደሚያስፈልጋቸው ይናገራል፡፡ በጎች የሚያስፈልጋቸውን የመንፈስ ቅዱስ ውሃ ካላገኙ ሌላ ውሃ ፍለጋ ወደተሳሳተ ሥፍራ ይሄዳሉ በማለት ያስረዳል፡፡ ይህም እያንዳንዱ እረኛ በጎቹን ሊያገለግልና የመንፈስ ቅዱስን ውሃ ሊያቀርብላቸው እንደሚገባ ያስተምረናል፡፡ አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባላት ለችግራቸው መፍትሔ ፍለጋ ወደ ባዕድ አምልኮና ወደ ጥንቆላ ኃይል ሲሄዱ የሚገኙት ከቤተክርስቲያን መድረክ በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ አገልግሎት በመታጣቱ ነው፡፡

ፊሊፕ ኬለር እንዲህ ይላል ፡-

> ሰውነታችን ውሃ መጠጣት እንደሚችልና እንደሚያስፈልገው ሁሉ የሰው ነፍስ የዘላለማዊውን አምላክ የእግዚአብሔርን መንፈስ ውሃ መጠጣት እንደምትችልና እንደሚያስፈልጋት የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያስረዳናል፡፡ በጎች በሚጠሙበት ጊዜ ይቅበጠበጣሉ፣ ውሃም ፍለጋም ይወጣሉ፡፡ ወደ መልካም ውሃ ካልተመሩ እንደ ጉበት ትል፣ የኮሶ ትል የመሳሰሉና ሌሎችም ጀርሞች ሊጠቁበት ከሚችሉበት *ከተበከለ የጉድጓድ ውሃ ሲጠጡ ይገኛሉ፡፡*
>
> ይህም በአንድ ወቅት ያየሁትን፣ እጅግ ወደሚያምር ተራራ እረኛቸው ሲመራቸው የነበሩ በጎችን ያስታውሰኛል፡፡ በውብ በዛፎች መካከል ይፈስ የነበረው ውሃ ከበረዶ እየቀለጠ የሚወርድ ኩልል ያለ ንፁህ ነበር፡፡ ነገር ግን በጎቹ በመንገዝ ላይ እያሉ ከመካከላቸው በርከት ያሉ እልከኛ ሴት በጎች ከነግልገሎቻቸው ወደ ንፁሁ ውሃ ከመሄድ ይልቅ ከቆጭኑ መንገድ ዳር ላይ

ከሚገኝ አነስተኛ፣ ቆሻሻና ጭቃማ ከሆነ ጉድጓድ ውሃ ለመጠጣት ቆሙ። ውሃው የቆሸሸው በበጎች ኮቴ በላቀጠ ጭቃ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በዚያ መንገድ ባለፉ የበግ መንጎች ሽንት ጭምርም ነበር። ያም ሆኖ ግን እነኚያ አመፀኛ በጎች ውሃው በአካባቢው ሊገኝ የሚችል የተሻለ ውሃ ያ ብቻ እንደሆነ እርግጠኞች ነበሩ።

ውሃው በራሱ ቆሻሻና እነሱን የማይመጥን ውሃ ነበር። ከዚያ በተጨማሪ ደግሞ ቀስ በቀስ በሆድ ውስጥ ትላትል እንዲሰቃዩና በጎጂ በሽታ እንዲጠቁ በሚያደርግ በጉበት ትልና በኮሶ ትል እንቁላሎች የተሞላ ነበር።

ለበጎች ሦስት የውሃ ማግኛ መንገዶች አሉ። ምንጭና ወራጅ ወንዝ፣ የሳር ላይ ጤዛ፣ እና ጥልቅ የጉድጓድ ውሃ ናቸው ። እንደበግ ያሉ እንስሳት ሰውነት በአማካይ 70 ፐርሰንት ያህሉ ውሃ ነው። ውሃ ለጤናማ ሥርዓተ አካል ይጠቅማል። ውሃ ለረቂቅና ጤናማ ለሆነው እንቅስቃሴያቸው አስተዋጽኦ ያለው የእያንዳንዱ ሴል አካል ነው።

ስለሆነም ውሃ የበጎችን ንቃት፣ጥንካሬና ብርታት የሚወስን ነው።

## ምዕራፍ 3

# መፈንገል በበጎች ላይ የሚያመጣው ጉዳት ምንድነው?

*"ነፍሴ ሆይ፥ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ..."*

መዝሙር 42፡11

ከበጎች ጋር ብዙ ጊዜ ያሳለፈው ባለፈው ምዕራፍ የተመለከትነው ዘመናዊው እረኛ በጀርባ መፈንገል ለበጎች ምን እንድምታ እንዳለው ይነግረናል። ከበጎች መካከል አንደኛው ያለ ረዳት ራሱን ችሎ መቆም ወደማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ማወቅ እጅግ የሚያስገርም ነው። በበጎችና በሰዎች መካከል ያለው መመሳሰል አስገራሚ ነው ቢባል አይገርምም።

ፊሊፕ ኬለር እንደ በጎች እንደነበሩትና ከበጎች ጋር እንደመስራቱ ልምዱን እንደሚከተለው ያካፍለናል፡-

ካስት ዳውን የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል (መተከዝ ተብሎ በአማርኛ የተተረጎመው) በጀርባው ተፈንግሎ ወድቆ መነሳት ያቃተውን በግ ለመግለጽ የበግ እረኞች ይጠቀሙበት የነበረ የቆየ የእንግሊዝኛ ቃል ነው። የተፈነገለ በግ ሲታይ በጣም የሚያሳዝን ነው። በጀርባው ተኝቶ እግሩ ወደ ሰማይ ተዘርግቶ ላይሳካለት እስኪላላጥ ድረስ ለመነሳት ሲፍጨረጨር ማየት አሳዛኝ ነው። አልፎ አልፎ የደከመ የእርዳታ ጩኸት እያሰማ በሚያስፈራ ተስፋ መቁረጥ ተጠፍሮ የሚውተረተር ምስኪን ፍጥረት ነው።

በጀርባው የተንጋለለ በግ የበጉ ባለቤት ቶሎ ካልደረሰለት ይሞታል። በዚህና በሌሎችም ምክንያት ነው ጠንቃቃ እረኛ በየቀኑ መንጋውን በጥንቃቄ መጠበቅና መቁጠር እያንዳንዱ በግ መነሳቱንና በእግሩ መቆሙን ማረጋገጥ ያለበት። አንድ ወይም ሁለት በጎች ከመንጋው መካከል ቢጎድል በእረኛው አዕምሮ ውስጥ ወዲያው የሚመጣው ሀሳብ ከበጎቹ መካከል አንዱ ተፈንግሏል፣

ሄጄ ልፈልገውና በእግሩ እንዲቆም ልረዳው ይገባኛል የሚል ነው፡፡

በተፈነገለ በግ ላይ አይኑን የሚጥለው እረኛው ብቻ ሳይሆን ነጣቂ አውሬም ነው፡፡ ጭልፊቶች፣ጥንብ አንሳዎች፣ ውሾች፣ ተኩላዎችን የመሳሰሉት በጀርባው የወደቀ በግ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚሞትና በቀላሉ ሊመገቡት እንደሚችሉ ያውቃሉ፡፡፡

በድካም ምክንያት በጀርባው የተንጋለለ በግ ረዳት የሌለው፣ ለሞት የቀረበ፣ እና ለጥቃት የተጋለጠ መሆኑ መታወቁ ለእረኛው የተንጋለለ በግ ጉዳይ በጣም አሳሳቢ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ትልልቅ፣ የሰቡ፣ ጠንካራ አንዳንዴም እጅግ ጤናማ በጎች ሳይቀሩ ሊፈነገሉና ለጥቃት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ ይህም እውነታ እረኛው በምንም ሳይዘናጋ ለመንጋው የማቋርጥ አገልግሎትና ትኩረት እንዲሰጥ ያደርገዋል፡፡ ለነገሩ በተደጋጋሚ የመውደቁ አደጋ በቀላሉ የሚያጋጥማቸው የሰቡ በጎች ናቸው፡፡

***በጎች የሚፈነገሉበት ሁኔታ እንዲህ ነው፦*** ክብደት ያለው የሰባ ወይም ረጅም ላት ያለው በግ በአነስተኛ ጉድባ ወይም ጉድጓድ ወስጥ ተመቻችቶ ይተኛል፡፡ ጥቂት እንደቆየም ዘና ለማለት ወይም ለመንጠራራት ብሎ ቀስ እያለ ወደ ጎን ይገለበጣል፡፡ ነገር ግን ሳያስበው የስበት ኃይል በጀርባው እንዲንጋለል ያደርገዋል፡፡ ወዲያውኑ ይደነግጥና መፈራገጥ ይጀምራል፡፡ ያ ግን የበለጠ ችግሩን ያባብሰውና ተነስቶ መቆም የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡

ከተጋደመበት ለመነሳት ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ በሆዱ ውስጥ ጋዝ ይፈጠራል፡፡ ይህ የሚፈጠረው ጋዝ እየጨመረ በሚሄድበት ጊዜ በሰውነቱ ውስጥ ያለውን የደም ዝውውር በተለይም ወደ እግሮቹ የሚሄደውን ደም ያዘገየዋል ከዚያም ሙሉ በሙሉ ያቆመዋል፡፡ የአየር ሁኔታው እጅግ ሞቃታማና ፀሃያማ ከሆነ በጉ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሊሞት ይችላል፡፡ ቀዝቃዛና ደመናማ ከሆነ ደግሞ ለተወሰኑ ቀናት በጀርባው እንደተንጋለለ በህይወት ሊቆይ ይችላል፡፡

እረኛው የጠፋበትን አንድ በግ ለመፈለግ ብዙ ሰዓታት ሊያጠፋ ይችላል፡፡ አንዳንዴ ከሩቅ በጀርባው ተንጋሎ ያለ ረዳት ሆኖ

ሊያየው ይችላል። ወዲያውም እያንዳንዷ ደቂቃ ወሳኝ መሆኗን በመረዳት በተቻለው ፍጥነት ወደ በጉ ይሮጣል። በዚህ ጊዜ በእረኛው ልብ ውስጥ የስጋትና የደስታ የተደባለቀ ስሜት ይፈጠራል። ፍርሃቱ ምናልባት በጉ አይተርፍ ይሆን በማለት ሲሆን ደስታው ደግሞ ምንም ቢሆን የጠፋውን በጉን በማግኘቱ የሚፈጠር ነው።

ወደ ወደቀው በግ በደረሰ ጊዜ እረኛው የሚያደርገው የመጀመሪያ ሙከራ በጉን ለማንሳት ነው። በቀስታ በጉን ወደ ጎን ይገለብጠዋል። ይህም በበጉ ሆድ ውስጥ የተፈጠረውን ጋዝ ግፊት ለማስወጣት ይረዳል። በጉ በዚያ ሁኔታ የቆየው ለረጅም ጊዜ ከሆነ እረኛው በጉ በእግሩ እንዲቆም አቅፎ ማንሳት ይኖርበታል። ከዚያም እረኛው በጉን በእግሮቹ መካከል አቁሞ ደም ወደየእግሮቹ እንዲደርስ የደም ዝውውሩን ለማነቃቃት የበጉን ጭኖች ያሻቸዋል። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ጥቂት ጊዜ የሚወስድ ነው። በጉ ተነስቶ ለመራመድ በሚሞክርበት ጊዜ ይወላከፋል፤ ይንገዳገዳል ደግሞ አሁንም እንደገና ይወድቃል። ቀስ በቀስ በጉ ሚዛኑን መጠበቅ ይችላል። በእርግጠኝነት ቀጥ ብሎ መራመድ ይጀምራል። እንዲህ እንዲህ እያለ ከፍርሃትና ከተስፋ መቁረጥ ነፃ ሆኖና ጥቂት ረዘም ላለ ጊዜ የመኖር ሌላ ዕድል ተጨምሮለት ወደ መንጋው ይቀላቀላል። በጎች በተለያየ ምክንያቶች ይፈነገላሉ፤

1. ለመተኛት የሚመች ለስላሳና ክብ ጉድጓድ የሚመርጡ በጎች አብዛኛውን ጊዜ የመፈንገል አደጋ ይገጥማቸዋል። በእንደዚህ አይነት አመቺ ሁኔታ ሲሆኑ በጀርባ ለመንጋለል በጣም ቀላል ነው።

በክርስትና ህይወት ምንም ችግር የሌለበት፤ ብዙ ትግል የማይጠይቅና ራስን መግዛት የማይጠይቅ ቀላል ቦታን መፈለግ አደጋ አለበት።

2. ብዙ ጠጉር በጎች እንዲፈነገሉ ያደርጋል። የበግ ጠጉር በጣም ረጅም ሲሆንና በጭቃ፤ በእበት እና በሌሎችም ቆሻሻዎች በሚከብድበት ጊዜ ለበጎች በቀላሉ መፈንገል ምክንያት ይሆናል። በገዛ ጠጉሩ ወደ ታች ተጎትቶ ይወድቃል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ‹‹የበግ ጠጉር›› በክርስቲያኖች ህይወት ላይ ተጣብቆ ያለውን አሮጌውን ማንነት ያመለክታል፡፡ ይህም በውጭ የሚገለጠው የውስጥ ማንነታችን፣ ፍላጎታችን፣ ተስፋችንና ምኞታችን ነው፡፡በዙሪችን ካለው አለም ጋር ያለማቋረጥ ግንኙነት የምናደርግበት የህይወታችን ክፍል ነው፡፡ የምድር ግላንግሶች፣ ምድራዊ ሀብት፣የሚከብዱና ወደ ታች የሚስቡ ምድራዊ ሀሳቦች የሚንጠለጠሉት በዚህ አሮጌ ማንነት ላይ ነው፡፡

ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገባ የበግ ጠጉር እንዲለብስ የተፈቀደለት ሊቀ ካህን እንደሌለ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም እኔነትን፣ ትዕቢትን፣ የራስ ጽድቅን የሚያመለክት ሲሆን እነዚህንም እግዚአብሔር እንደማይታገስ ያሳስበናል፡፡

አንድ በግ በጠጉሩ ርዝመትና ክብደት ምክንያት የመፈንገል አደጋ በሚገጥመው ጊዜ እረኛው ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ፈጣን እርምጃ ይወስዳል፡፡ በጉን የመሸለት እርምጃ ይወስዳል፡፡ በደንብ አድርጎ በመሸለት በጉ ከሞት አደጋ ነፃ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በጎች በመሸለት አይደሰቱም፡፡ ይህ ለበጎች የሚያስደስት እርምጃ አይደለም፡፡ ለበጎች መሸለት የሚያዝናና ጉዳይ አይደለም፡፡ ለእረኛው ደግሞ አድካሚ ሥራ ነው፤ ሆኖም ግን መደረግ አለበት፡፡

3. በጣም መሰባት በጎች እንዲፈነገሉ ያደርጋል፡፡ ከመጠን በላይ የሰቡ በጎች ጤናማ ያልሆኑና ፍሬያቸውም ብዙ እንዳልሆነ የታወቀ ነው፡፡ ደግሞም በተደጋጋሚ የመፈንገል አደጋ የሚገጥማቸው የሰቡ በጎች ናቸው፡፡ክብደታቸው በቀላሉ በንቃትና በቅልጥፍና እንዳይራመዱ ያደርጋቸዋል፡፡ እረኛው በጎቹ እየሰቡና ለመፈንገል አደጋ ወደመጋለጥ እየተቃረቡ መሆኑን ከተጠራጠረ ችግሩን አስቀድሞ ለማስወገድ ዘላቂ እርምጃ ይወስዳል፡፡ ከበፊቱ ያነሰ ሣር ወደሚመገቡበትና አጠቃላይ ሁኔታቸው በቅርብ ክትትል ሥር በሚሆኑበት የተመጠነ አመጋገብ ሥርዓት ውስጥ እንዲቆዩ ያደርጋቸዋል፡፡ የእረኛው ዓላማ በጎቹ ጠንካራ፣ብርቱ፣ ጉልበታም እንጂ የሰቡ፣ ልፍስፍስና ደካማ እንዳይሆኑ ማድረግ ነው፡፡

## ምዕራፍ 4

# በጎች መመራት የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።
በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።
ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።"

መዝሙር 23፡1-3

ያለ ምሪት የቤተ ክርስቲያናችን አባላት መረን ይሆናሉ፣ ህይወታቸውም ይበላሻል። ብዙ ሰዎች በውስጣቸው የተተከለ ጎጂ የህይወት ዘይቤ አላቸው። ልምዱን እያካፈለን ያለው ዘመናዊው እረኛ በጎች እንዴት ምሪት እንደሚፈልጉ ይነግረናል። በጎች ለገዛ ራሳቸው ከተተው ይቅበዘበዛሉ፣ አሉታዊ በሆነ ሊያጠፋቸው በሚችል አካሄድ ራሳቸውን ይጎዳሉ በማለት ያስረዳል። በመቀጠልም፦-

‹በጎች የትም ሊሰማሩ ይችላሉ› የሚለው አባባል ብዙ የተለመደ ነገር ግን ስለበጎች የተሳሳተ አመለካከት ነው። እውነታው ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው። *እንደበጎች ያለ ጥንቃቄ የሞላው አያያዝና ዝርዝር ምሪት የሚፈልግ ሌላ እንስሳ የለም።* በጎች ፍፁም ማስተዋል በጎደለው መንገድ አንዱ ሌላውን ዝም ብሎ እየተከተለ መንገዱ ከሥራቸው እስኪጎደጉድ ድረስ በአንድ መስመር እንደሚሄዱ ሁሉ እኛም ሰዎች ወደ ጥፋት ያመጡንን ልማዶች ሙጭጭ አድርገን እንይዛለን።

"እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።"

ኢሳይያስ 53፡6

በጎች ጥንቃቄ በተሞላበት አያያዝ መተዳደር አለባቸው። ለገዛ ራሳቸው ከተተዉ በራሳቸውም መንገድና በማይጠቅም ልምዳቸው መነዳት ይጀምራሉ።

1. *ያለ ምሪት በጎች መሬቱ እስኪጎደጉድ ድረስ አንድ መስመር ብቻ ተከትለው ነው የሚግጡት።* በዚህም ሁኔታ ሥሩ

እስኪጎዳ ድረስ ይግጡታል። ይህም ሥሩ ተጎትቶ ስለሚወጣ ሥፍራው ለምድረበዳነት ይጋለጣል። እንዲህ ያለው አግባብ የሌለው የግጦሽ መሬት አጠቃቀም የመሬቱን ለምነት ከመጉዳቱም በላይ መሬቱን ለከፍተኛ መሸርሸር ይዳርገዋል።

2. ያለ እረኛ የሆኑ በጎች ሥፍራው ወደ ምድረበዳነት እስኪቀየር ድረስ ከአንድ ቦታ ብቻ ነው የሚግጡት። መቼውንም ቢሆን በጎች ሲከሱ ሲጎዱና ህመምተኛ ሲሆኑ ለመሬቱም ሆነ ለበጎቹ ባለቤት ኪሳራ ነው።መንጋውን በሚያሰማራበት ጊዜ አንድ እረኛ ሊያደርገው የሚችለው ዋናውና ብቸኛው ጥንቃቄ በጎቹን ለግጦሽ ከቦታ ወደ ቦታ ማዘዋወር ነው። ከጊዜ ወደጊዜ ከአንዱ ግጦሽ ወደ ሌላ ግጦሽ ወደ ሌላ ግጦሽ መዘዋራቸው ግድ ነው።

3. ያለ እረኛ በጎች አካባቢያቸውን በበሽታና በበሽታ አምጪ ተዋሲያን ይበክላሉ። ከበጎች ባህሪና የተወሰኑ የተመቹ ቦታዎች ከመምረጣቸው የተነሳ በመልካም እንክብካቤ ተይዘው የነበሩ ቦታዎች በፍጥነት በተለያዩ ጥገኛ ህዋሳት ይበከላሉ። ስለዚህም በአጭር ጊዜ ውስጥ መንጋው በሞላ በትላትሎችና ቀንድ አውጣዎች ይጠቃል።

## አንድን እረኛ እየተከተልክ ስለመሆኑ የሚያመላክቱ ሰባት ምልክቶች፡-

1. ብልጽግና፡- በእረኛ እየተመራህ ስለመሆኑ የሚያሳየው የመጀመሪያው ምልክት ብልፅግና ነው። የጌታን ድምጽ ወደሚሰማ ሰው ብልፅግና ሁልጊዜ ይመጣል።

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።"

መዝሙር 23፡1

2. እረፍት፡- በእረኛ እየተመራህ እንደሆነ የሚያመለክተው ሁለተኛ ምልክት ጸጥታ፣ እረፍትና ደህንነት ነው።

"...በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።"

መዝሙር 23፡2

3. መንፈሳዊ ምግብ ፡- በእረኛው እንክብካቤ ሥር ያለ ሰው በእግዚአብሔር ቃል የተሞላ ነው።

"በለመለመ መስክ ያሳድረኛል..."

መዝሙር 23፡2

4. መጽናናት፡- መጽናናት ከእረኛህ ጋር በመጣበቅ የምታገኘው ሌላው በረከት ነው።

"በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።"

መዝሙር 23፡4

5. ቅባት፡- እረኛቸውን የሚከተሉ ሰዎች ይቀባሉ። ቅባት ጌታን በትክክል የመከተልህ ምልክት ነው።

"...ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።"

መዝሙር 23፡5

6. ምህረትና ቸርነት፡- እረኛህን የምትከተል ከሆነ መልካም ቸርነትና ምህረት የሞላባቸውን ስጦታዎች በህይወትህ መጠበቅ አለብህ። በህይወትህ የምትለማመደው ምህረትና ቸርነት እረኛህን ለመከተልህ ምልክቶች ናቸው።

"ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል...።"

መዝሙር 23፡6

7. ዘላለማዊ ደስታ ፡- ዘላለማዊ ደስታ እረኛቸውን የሚከተሉ ሰዎች እድል ፈንታ ነው።

"...በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።"

መዝሙር 23፡6

*ምዕራፍ 5*

# በጎች የለመለመ መስክ የሚፈልጉት ለምንድነው?

*"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።*

*በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።"*

*መዝሙር 23፡1-2*

አሁንም እንደገና እስካሁን ስለ በጎች እየነገረን ያለው ያ ዘመናዊ እረኛ በጎች ለግጦሽ የለመለመ መስክ እንዴት እንደሚፈልጉ ይነግረናል። የአንድ እረኛ ጉብዝና ለበጎቹ የተለያዩ መመገቢያ መስክ በማዘጋጀት ብቃቱ ላይ ነው። ከተናገረው ውስጥ የሚከተለውን እጠቅሳለሁ፡-

በመጀመሪያ አስቀድሞ የተዘጋጀ መርሀ ግብር መኖር አለበት፣ ትክክለኛ የአመራር መርሀን የተከተለ ታስቦበት የተዘጋጀ ከአንድ ግጦሽ ወደ ሌላ ግጦሽ በየተራ ለመዘዋወር የሚያስችል ዕቅድ ያስፈልጋል። የበጎቹ ባለቤት ስምና ዝና ወደ ተሟላ አዲስና ትኩስ ሣር ወዳለበት ቦታ ውጤታማ በሆነና ብቃት ባለው መንገድ በጎቹን በማሰማራት ብቃቱ ላይ የተመሰረተ ነው። ዳዊት በጽድቅ መንገድ ስለመመራቱ ሲናገር በአዕምሮው የነበረው ይህ ነው።

እረኛ የማሰማሪያ መስኩን በሚገባ የሚያውቅ መሆን አለበት። ያተደጋጋሚ ሥፍራውን በሙሉ ማየት ይኖርበታል። የመስኩን ጥቅምና ጉድለት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። መንጋው ወዴት እንደሚሰማራ እንዲሁም ደግሞ ወደ መልካም ሣር ይመራቸው ዘንድ ሣር የማይገኝበትንም ቦታ ማወቅ አለበት። እረኛው ወደ ለመለመ መስክ የሚወስደውን አዲስ በር በሚከፍትበት ጊዜ ሁሉ በጎች በደስታ ይሞላሉ። በበሩም በሚያልፉበት ጊዜ የደከሙና ያረጁ በጎች እንኳ መልካም ሣር ማግኘታቸው ከሚሰጣቸው ደስታ የተነሳ እግራቸውን ወደላይ እያነሱ መዝለል ይጀምራሉ። ወደ ለመለመ አዲስ መስክ መሠማራት እንዴት ያስደስታቸዋል!

የማለዳው እርጋታና ጸጥታ፤ የበጎቼ እግር በለመለመ ሣር ተሸፍኖ ሳገኛቸው፤ ከዚያም በሚፈልጉትና በተሟላ መልኩ ሲመገቡ፤ ፀሐይ ስትወጣና በቅጠሎች ላይ ያለውን እርጥበት ማድረቅ ስትጀምርና በጎች ጥላ ፍለጋ ሲሄዱ፤ ከዚያም ተዝናንተውና ደስ ብሏቸው ተኝተው ቀኑን ሙሉ ሲያመነዥኩ በአይነ ህሊናዬ አስባለሁ። ይህን እንደማየት የሚያስደስተኝ ነገር የለም።

## ምዕራፍ 6

# በጎች በሸለቆዎች መካከል ማለፍ የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?

"በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፤ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።"

መዝሙር 23፡4

እያንዳንዱ ተራራ ሸለቆዎች አሉት። በፈፋ፣ በገደላገደሎችና በሸንተረሮች የተሞላ ነው። ሁልጊዜ ከሁሉ የተሻለ ወደ ተራራው ጫፍ ሊያደርስ የሚችለው መንገድ ደግሞ በእነዚህ ሸለቆዎች በኩል ነው። ደጋማ አገር የሚያውቅ ማንኛውም እረኛ ይህን በደንብ ያውቃል። ጠመዝማዛ በሆኑት ጨለማ ተራሮች መካከል በዝግታና በጽናት መንጋውን ይመራል። ከላይ ያነበብነው ጥቅስ "በሞት ጥላ መካከል እንኳን ባልፍ" አለ እንጂ እዚያው እሞታለሁ ወይም እገታለሁ አላለም። ይልቁኑ "በውስጡ አልፋለሁ" ነው የሚለው።

ዘመናዊው እረኛችን ከበጎች ጋር ካለው ልምድ በመነሳት በጎችን በሸለቆዎች መካከል እንዲያልፉ ማድረግ ለምን እንደሚያስፈልግ ያብራራል። እረኞች በጎቻቸውን በከፍታ ቦታዎች ብቻ ሳይሆን በሸለቆ ውስጥም እንደሚያሳልፏቸው ማወቅ በጣም አስገራሚ ነው። ብዙዎቻችን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ በከፍታ ብቻ ነው የሚመራን ብለን እናስባለን። ነገር ግን ሸለቆ በህይወታችን የምንዝልባቸውን ጊዜና ወቅቶች የሚያመለክት ነው።

እረኛው በጎቹን በጨለማውና በሚያስፈራው ሸለቆ ውስጥ አሳልፎ እንደገና ወደ ከፍታ ሥፍራ እንደሚያወጣቸው እንጂ በሸለቆ ውስጥ እንደማይተዋቸው ተመልክተናል። ይህ የኛን ህይወት በትክክል የሚገልጽ አይደለምን? በጨለማና አስፈሪ ሸለቆዎች ውስጥ ስንት ጊዜ አልፈናል? በእነዚያ ወቅቶች ያጸናን የእረኛችን ድምፅ ብቻ ነበር። የቤተክርስቲያን አባላት ምን ያህል ጊዜ በመጋቢያቸው ማፅናናትና ጥንካሬ ላይ ተደግፈዋል?

እስኪ አሁንም አንዳንድ የእረኝነት ምሳሌዎችን ልምድ ካለው ከዚያ እረኛ ልጥቀስ፡፡ እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

1. አብዛኞዎቹ ስኬታማ እረኞች በበጋ ወቅት ጥሩ ሣር ፍለጋ በጎቻቸውን ረጅም ርቀት ለመውሰድ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ይሕም ረጅም ርቀትን መጓዝ ይጠይቃል፡፡ በጎቹ እግረ መንገዳቸውን ሣር እየጋጡ፣ በበረዷማው ተራራ ላይ እየወጡና እየወረዱ በዝግታ ይጓዛሉ፡፡ ፀደይ እየቀረበ በሚመጣበት ጊዜ በረዶ በተራራው ጫፍ ላይ መከመር ስለሚጀምር በጎቹ ቀስ በቀስ ከተራራው ለመውረድ ይገደዳሉ፡፡ በመጨረሻም የበልግ ወራት በሚያልፍበት በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ በጎቹ ክረምቱን ወደሚያሳልፉበት እንደ ሰንሠለት ተያይዞ ወደተሰራው ጋጣቸው ይመለሳሉ፡፡

   ይህ ወቅት መንጋው ሙሉ በሙሉ ከእረኛው ጋር ብቻ የሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ ከእረኞቻቸው ጋር በቀረበ ግንኙነትና የሌት ተቀን ክትትል ውስጥ ይሆናሉ፡፡

   ተራራ ሁሉ ሸለቆዎች አሉት፡፡ ተራራ በተለያዩ ፏፏዎችና ሸንተረሮች የተሞላ ነው፡፡ ስለሆነም ወደ ተራራው ጫፍ ለመውጣት የሚሻለው መንገድ በሸለቆዎቹ በኩል ነው፡፡ ደጋማ አካባቢን በደንብ የሚያውቅ እረኛ ይህን በደንብ ያውቃል፡፡ በዚያ ነፋስ ሰንጥቆ በሚያልፍበት ሸለቆ መንጋውን በእርጋታ ነገር ግን ደግሞ በጽናት ይመራል፡፡ ‹‹በሞት ጥላ መካከል እንኳ ባልፍ›› የሚለውን ጥቅስ በሚገባ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ባልፍ አለ እንጂ እዚያው እቀራለሁ ወይም እሞታለሁ አላለም፡፡

2. በሕይወታችን ሸለቆዎች ውስጥ ከራሱ ከእግዚአብሔር ተሀድሶን እናገኛለን፡፡ በከባድ መከራ ውስጥ ከእርሱ ጋር አብረን እስካልተራመድን ድረስ በዚያ በመከራችን ውስጥ እያለን እርሱ በአጠገባችን ሆኖ በእርሱ ወደሆነ ወደ እረፍት እንደሚመራን ልንረዳ አንችልም፡፡ በእንደዚህ አይነት ልምምድ ውስጥ ላላለፈ ይህን ለማመን ያስቸግረዋል፡፡

3. በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ያሉትን ማጽናናትና ማበረታታት የሚችሉት በእንዲህ ያሉ ጨለማ ሸለቆዎች ውስጥ ያለፉ

ብቻ ናቸው፡፡ ብዙዎቻችን በህይወታችን ሸለቆ እንዲገጥመን አንፈልግም፡፡ ከፍርሃትና ከሥጋት የተነሳ ከእነርሱ ገሸሽ እንላለን፡፡ ነገር ግን ከኛ ጥልቅ ስጋት አልፎ እግዚአብሔር በሸለቆዎቻችንን በሁል ታላቅ ጥቅምና ዘላቂ በረከትን ወደ ሌሎች ማምጣት ይችላል፡፡

4. እረኛው በጎቹን በሸለቆዎች መካከል የሚመራበት ምክንያት በጣም የተሻለ መልካም ሳር በዚያ ስለሚገኝ ነው፡፡ መንጋው በዝግታ ይጓዛል እንጂ አይጣደፍም፡፡ ጠቦቶቹ በዚያ አይነት መንገድ አልፈው አያውቁም፡፡ እረኛው ውሃ ብቻ ሳይሆን ሴት በጎች ከጠቦቶቻቸው ጋር የሚመገቡት መልካም ሣር መኖሩን ያረጋግጣል፡፡ ባጠቃላይ ምርጡ መስክ የሚገኘው በሸለቆዎቹ መካከል ወራጅ ውሃውን ተከትሎ ነው፡፡ በጎቹ ወደ ተራራማው አገር እየተጓዙ እግረ መንገዳቸውን ይመገባሉ፡፡

*ምዕራፍ 7*

# አልጠግብ ባይ በጎች ምን ያጋጥማቸዋል?

የዘመናዊ እረኛ አንድ በግ እንዴት አልጠግብ ባይ ሌሎችን በጎችም እንደሚበጠብጡ ይገልጻል፡፡ በእውነተኛ በጎች ላይ የሚታየው መስያየትን መፍጠር፣አልጠግብ ባይነትና ግራ መጋባት መጋቢዎች በሚመሯቸው «የሰው በጎች» ላይ በሚታየው ተመሳሳይ ሁኔታ መደናገጥ እንደሌለባቸው ያስተምራቸዋል፡፡ የበጎች እረኛ በበጎች መካከል ግራ መጋባትን የሚፈጥረውን በግ የሚዳኝበት «አስቸጋሪውን በግ አርዶ ለእራት ማዘጋጀት!» ማዘጋጀት የሚል መመሪያ አለው፡፡ ይህም ለመጋቢዎቹ ሁሉ የሚሆን መገለጥ ነው፡፡

እስኪ ከዘመናዊ እረኛ ትምህርት እንውሰድ፡፡ *መዝሙር 23 በእረኛው ዓይን* ከተሰኘው መጽሐፉ የተወሰደ ጥቂት ሀሳብ እነሆ፡፡

> “እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም፡፡” (*መዝሙር* 121፡4)
>
> እንዲህ ያለ ጌታና ባለቤት እያላቸው ብዙ ክርስቲያኖች በእርሱ አመራር ሥር እርፍ ብለው፣ በአብዛኛው እርካታ የላቸውም፤ ከአጥር ውጭ ያለው ሣር የበለጠ ልምላሜ ያለው እንደሆነ ያስባሉ፡፡ እነኚህ ከሁለቱም ዓለሞች የሚፈልጉ «በአጥር ሾላኪዎች» ወይም «ግማሽ ክርስቲያኖች» ተብለው ሊጠሩ የሚገባቸው ሥጋዊያን ክርስቲያኖች ናቸው፡፡
>
> በአንድ ወቅት እንዲህ ያሉ ክርስቲያኖች የሚያሳዩትን ባህሪ የሚመስል ባሕሪ የምታሳይ ሴት በግ ነበረችኝ፡፡ እጅግ ውብ ከምላቸው በጎቼ መካከል አንዷ ነበረች፡፡ የሰውነቷ ቅርጽ ያማረና የተስተካከለ ነበር፡፡ መልካም ቁመናና ምርጥ የበግ ሱፍ የለበሰች ነበረች፡፡ የፀዳ፣ ንቁና በመልካም ዓይኖች የተዋበ ራስ ነበራት፡፡ በፍጥነት ያደጉ ጠንካራ ግልገሎችን ወልዳ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሁሉ የሚስብ ነገር እያላት አንድ የጎላ ችግር ነበረባት፡፡ እረፍት የለሽ ቅብጥብጥና በአጥር ሾላኪ ነበረች፡፡

በመንጋው ውስጥ ያሉት በጎች ከሚፈጥሩት ችግር ይልቅ ይህች አንድ በግ የምትፈጥርብኝ ችግር የከፋ ነበር። ወደየትኛውም መስክ ወይም ግጦሽ ቦታ እንግባ ወዲያውኑ ወደሌላ ግጦሽ የሚያስኬድ በአጥሩ ዙሪያ ወይም የባህር ዳርቻ (በባህር አካባቢ እንኖር ስለነበረ) ማምለጫ ቀዳዳ መፈለግ ትጀምራለች። ይህን የምታደርገው እዚህ በቂ ሳር ስላጠች አይደለም። የኔ የግጦሽ ቦታ እጅግ የሚያስደስተኝና እጅግ የሚያረካኝ ነው። ከኔ በጎች የተሻለ የግጦሽ ቦታ ያላቸው በጎች በአካባቢው አልነበሩም።

ይህ አልጠግብ ባይነት ከበጊቷ ጋር የተጣበቀ ልማድ ነበር። በምንም ነገር በቀላሉ አትረካም። ብዙ ጊዜ በአጥሩ ዙሪያ ቀዳዳ ወይም አጥሩ ዝቅ ያለበት ቦታ ወጥታ ራቅ ያለ ቦታ የደረቀ፣ የጠወለገ ወይም የተቃጠለ ሣር ስትበላ ትገኛለች።አንድም ጊዜ ግን ከስህተቷ ተምራ አታውቅም፤ በተደጋጋሚ ከአጥሩ ሾልካ ትወጣለች።

ይህ ድርጊቷ በራሷ ላይ የሚያበቃ ቢሆን ምንም አልነበረም። ከአስቸጋሪነቷ እንድትመለስ ለማድረግ መሞከር ይቻላል። ችግሩን የከፋ የሚያደርገው ያንኑ ተንኮሏን ለግልገሎቿም ማስተማሯ ነው። በቀላሉ የእርሷን ምሳሌ ተከትለው ልክ እንደርሷ ከአጥር ውጭ በመጥፋት የተካኑ ይሆናሉ።

ከዚህ የከፋው ግን ለሌሎች በጎች መጥፎ ምሳሌ መሆኗ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሌሎችን በጎች በለመደችው መሹለኪያ ቀዳዳ፣ አደገኛ በሆነ የባህር ዳርቻ በኩል አስከትላ ስትወጣ ትገኛለች።

የበጋውን ወራት ይህን ጠማማነቷን ከታገስኩ በኋላ በመጨረሻ መንጋውን ከመናወጥ ለማዳን እሷ መወገድ እንዳለባት ወሰንኩ። አንድ ችኮ፣ አልጠግብ ባይ በግ የመላውን መንጋ እንቅስቃሴ እንድታውክ መፍቀድ አልቻልኩም።

ከሌሎች በጎች እኩል ስለምወዳት ይህ ለኔ ከባድ ውሳኔ ነበር። ጥንካሬዋ፣ ውበቷና ንቃቷለማየት የሚያስደስት ነበር።

ነገር ግን አንድ ጠዋት ቢላ ወስጄ አረድኳት። በአጥር የመሹለክ ታሪኳ ተደመደመ። ለተፈጠረው ግራ መጋባት የነበረው ብቸኛ አማራጭ ይኸው ነበር። በጊቱ የትኛውንም የተሻለ እንክብካቤ ባደርግላትም አልጠግብ ባይ ነበረች።

# ምዕራፍ 8

# በትር ለበጎች ምን ይጠቅማል?

"በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፣ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።"

መዝሙር 23፡4

ዘመናዊው እረኛ ፊሊፕ ኬለር ለእረኞች በትር ዋና መሳሪያ እንደሆነ ያስረዳል፡፡በትር የሰው ልጆችን የሚያቀናውን የእግዚአብሔርን ቃል ያመለክታል፡፡ እርሱም የእረኞች ሥልጣንና ኃይል ብቸኛው መሠረት ነው፡፡ አንድ መጋቢ ለእግዚአብሔር ቃል ታላቅ አክብሮት ሊኖረውና የአገልግሎቱ ዋና መሣሪያ አድርጎ ማየት" ይኖርበታል፡፡

በትር ለበጎች እረኞች የሚሰጠውን ጥቅም የእግዚአብሔር ቃል ለቤተክርስቲያን መጋቢዎች ይሰጣል፡-

1. በትር እረኛው ራሱንና መንጋውን ከጥቃት ለመከላከል የሚተማመንበት መሳሪያ ነው፡፡
2. በትር እረኛው ከመስመር የሚወጡና የሚቅበዘበዙ በጎችን ለመመለስ እና ለመገሰፅ የሚጠቀምበት መሳሪያ ነው፡፡
3. በትሩ ለእረኛው ኃይሉና ጉልበቱ ነው፡፡
4. በትሩን በሠለጠኑት የእረኛው እጅ ውስጥ በማየት ውስጥ መጽናናትና እረፍት አለ፡፡ በጎች የእረኛቸው በትር የሁልጊዜ መፅናኛቸው እንደሆነ እርግጠኞች ናቸው፡፡
5. በትር እረኛው በጎቹን ለጥቅማቸው የሚገስጽበት መሳሪያ ነው፡፡
6. በትር እረኛው የበጎቹን ሁኔታ ለመፈተሽ ከቁጥር አለመጉደላቸውን ለማረጋገጥ ይጠቀምበታል፡፡ "ከበትርም በታች አሳልፋችኋለሁ ወደ ቃል ኪዳንም እስራት አገባችኋለሁ" (ሕዝቅኤል 20፡37) "ከበትር በታች" ማለፍ በእረኛው ቁጥጥርና ሥልጣን ሥር መሆንን ያመለክታል፤

ጥንቃቄ የሞላው፣ በፍቅር ለሆነና በእጁ ለሚደረግ የእረኛው ግምገማ ራስን ማስገዛት ነው:: በጎች ከእረኛው ‹‹በትር በታች›› በሚያልፉበት ጊዜ እረኛው በጥንቃቄ እየቆጠራቸውና በመልካም ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን እያረጋገጠ ነው ማለት ነው::

7. የእረኛው በትር እርሱም ሆነ በጎቹ አደጋ በሚያጋጥማቸው ጊዜ የሚከላከልበት መሳሪያው ነው:: ማንኛውንምጥቃት ለመመከትና ለመከላከል ያገለግላል::

## ምዕራፍ 9

# ምርኩዝ ለበጎች ያለው ጥቅም ምንድነው?

**"በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፣ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።"**

መዝሙር 23፡4

ዘመናዊው እረኞችን በበትርና በበምርኩዝ መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዳናል። በትር የሥልጣን፣የኃይል፣የተግሳፅ፣ እና ከአደጋ የመከላከል ጽንሰ ሀሳብ ያለው ሲሆን ምርኩዝ ደግሞ መከራን ስለመታገስና ስለቸርነት ይናገራል በማለት ያስረዳል። የበጎች ምርኩዝ ብዙ ጊዜ በአንድ በኩል ጫፉ ላይ የተቆለመመረጅምና ቀጭን እንጨት ነው። ባለቤቱ በጥንቃቄ የሚመርጠው እንጨት ነው። ባለቤቱ በሚፈልገው መልኩ አስተካክሎ የሚቀርጸው፣ የሚያለሰልሰውና የሚቆርጠው እንጨት ነው። ምርኩዝ የመጽናናትና የጥንቃቄ ምልክት ነው። እረኛው ለበጎቹ ያለውን ርህራሄ ያመለክታል።

ፊሊፐ ኬለር እንዲህ ይላል፡-

> በጎች ግትር ፍጥረት በመሆናቸው ብዙ ጊዜ ትርጉም ወደሌለውና ወደማይረባ ግራ መጋባት ውስጥ ይገባሉ። የገዛ በጎቼ ለአንድ ጉርሻ ሣር ተስገብግበው ወደ ገደል አፋፍ ሲሄዱና አንሸራቷቸው ወደ ባህር ሲወድቁ ተመልክቻለሁ። በረጅሙ ምርኩዜ ብቻ ነው ልጎትታቸውና ወደ መሬት ላወጣቸው የምችለው። በአንድ ክረምት ወቅት ብዙ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ነገር ያጋጥማት የነበረችን በግ ለማውጣት በርካታ ሰዓታት እንደፈጀብኝ አስታውሳለሁ። ወደ ጥፋት የሚከታት የራሷ ግትርነት ነው።
>
> ሌላው አጋጣሚ ደግሞ በጎች ለጥቂት ሣር ብለው ቆንጥርና ጥሻ ውስጥ ገብተው የሚተበተቡበት ሁኔታ ነው። ወዲያውኑ እሾሁ በጠጉራቸው ላይ ተሰግስጎ ይይዛቸውና ከዚያ ለመውጣት ይሳናቸዋል። ምርኩዝን በመጠቀም ብቻ ነው ከተጠላለፉበት ማውጣት የሚቻለው።

ይህ በእኛም የሚሆን ነው። ብዙዎቹ እንቅፋት የሚሆኑብንና የሚያግዱን ነገሮች ራሳችን የፈጠርናቸው ናቸው። በግትርነት፣ በገዛ ፈቃድ፣ በራስ መንገድ ተገፍተን ራሳችንን በቀላሉ ልንላቀቀው ወደማንችል ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። ወዲያውኑ እረኛችን በእርጋታ፣ በርህራሄና በጥንቃቄ ወደኛ ይመጣለል። ወደኛ ቀረብ ብሎ ከገባንበት አስቸጋሪ ሁኔታና ግራ መጋባት ለሰስ አድርጎ በመንፈስ ቅዱስ ያወጣናል። እግዚአብሔር ለኛ ያለው ትዕግስት እንዴት ታላቅ ነው! ትእግስቱና ርህራሄው እንዴት ግሩም ነው! ይቅርታው እንዴት ብዙ ነው!

ምርኩዝህ ያጽናናኛል! ክርስቶስ ሆይ መንፈስህ መጽናኛዬ ነው።

1. **እረኛው ምርኩዙን በጎቹ የተቀራረበ ግንኙነት እንዲኖራቸው በአንድ ላይ እንዲሰባሰቡ ለማድረግ ይጠቀምበታል። አዲስ የተወለደ ግልገል ከእናቱ ርቆ ካለ እረኛው ግልገሉን በጥንቃቄ ወደእናቱ ለማቅረብ ምርኩዙን ይጠቀማል። ምርኩዙን የሚጠቀምበት ምክንያት ግልገሉን በእጁ ከነካውና የእጁ ሽታ በግልገሉ ሰውነት ላይ ቀርቶ እናትየው ግልገሏን እንዳታገለው ለመጠንቀቅ ነው።**

2. **እረኛው ምርኩዙን ከበጎቹ መካከል አንዳንድ በጎችን (ወጣት ወይም ያረጁ ሊሆኑ ይችላሉ) ደህንነታቸውን በሚገባ ለመፈተሽ ወደራሱ ለማቅረቢያ ይጠቀምበታል። በዚህም ረገድ አይን አፋር የሆኑ ከእረኛቸው ራቅ ብለው የሚራመዱ በጎች ከምርኩዙ የተነሳ አገልግሎት ለማግኘት ይበቃሉ።**

3. **ብዙ ጊዜ እረኞች በትራቸውን በጎችን በአደገኛና በአስቸጋሪ መንገድ በጎቻቸውን ወደ አዲስ አቅጣጫ ለመምራት ይጠቀሙበታል። በጎቹን ለመግረፍ አይጠቀምበትም። ይልቁኑ እረኛው የምርኩዙን ጫፍ ከበጉ አንድ ጎን ላይ ያሳርፍና ወደሚፈልገው አቅጣጫ ይገፋዋል። ይህም በጎች በትክክለኛ መንገድ ላይ እንዳሉ እርግጠኞች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።**

## ምዕራፍ 10

# በጠላቶቻቸው ፊት ለፊት ገበታን ማግኘት ለበጎች ያለው ትርጉም ምንድነው?

ህይወታችንን የምንኖረው በጠላቶቻችን ፊት ለፊት እንደሆነ እሙን ነው። ሠይጣን ጠላታችን ነው ደግሞም ሁልጊዜ እኛን የሚጥልበት ዕድል የሚያስችለውን መግቢያ ቀዳዳ ይፈልጋል። እያንዳዱ እንቅስቃሴህን ጠላት ይከታተለዋል ብሎ ማሰብ የተለመደ አይደለም። እቤት ውስጥ ሆነህ፣ በግል ክፍልህ ውስጥ፣ ቴሌቭዥን በምትመለከትበት ጊዜ በዚህ ሁሉ እነኛ ክፉ አይኖች አንተ ላይ ያነጣጥራሉ። ይህ በምድር ላይ የሚኖር ሰው ሁሉ ዕጣ ፈንታ ነው። ጠላትህ ሊያይህ ይችላል አንተ ግን አታየውም! የበጎቹን ህይወት በሚገባ መጠበቅ የእረኛው ዐቢይ ተግባር ነው። የበጎቹን ህይወት መታደግ የሚችለው የመልካም እረኛ ንቁ ትጋት ብቻ ነው።

የእረኝነትን ጥበብ በተግባር የሚያውቀው ፊሊፕ ኬለር ስለዚህ ጉዳይ የሚለው ነገር አለው፡-

> ንቁ እረኛ የሚያከናውነው ሌላ ተግባር ደግሞ ነጣቂ አውሬዎችን በንቃት መጠበቅ ነው። የተኩላዎችን፣ የአነሮችንና ድቦችን ምልክትና ሽታ ያነፈንፋል። እነኚህ አውሬዎች በጎቹን ከወረሩ ወይም ካወኩ እረኛው ሊያድናቸው ወይም በጎቹ በሰላም ያርፉ ዘንድ ከአውሬዎቹ ጋር ስቃይ የሞላው ትግል ያደርጋል።
>
> *ብዙ ጊዜ የሚሆነው እንዲህ ነው፦ እነኚህ ተንኮለኛ አውሬዎች ፈጣን የደፈጣ ጥቃት ለማድረስ የሚያስችላቸው ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ የበጎቹን እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ቋጥኝ ላይ ወጥተው ይከታተላሉ። ከዚያም ከመንጋው ውስጥ አንዱ በአውሬዎቹ ስል ጥርስና ጥፍር ውስጥ ይገባል።*
>
> ይህ ትዕይንት በድራማ፣ በእንቅስቃሴ፣ በልብ አንጠልጣይ ክስተት እና ምናልባትም በሞት የተሞላ ነው። ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉትን አውሬዎች በግልጽ ለያይ በሚችልበት ቦታ ላይ ለመንጋው መብልን የሚያዘጋጅ ንቁ እረኛ ብቻ ነው በጎቹን

ከአውሬ ጥቃት ሊታደግ የሚችለው። ለእንዲህ ዓይነቱ አስቸጋሪ ሁኔታ የሚያደርገው ቅድመ ዝግጅት ብቻ ነው በጎቹን በአውሬዎች እንዳይታረዱና በስጋት እንዳይሙቱ የሚያደርጋቸው።

አሁንም እንደገና እዚህ ላይ የጠላታችን የሠይጣንንና የጭፍሮቹን ተንኮልና ክህደት በሚገባ ስለሚያውቀው ስለአዳኛችን ትምህርት እናገኛለን። እኛ ሁልጊዜ በጥቃት አደጋ ላይ ነን። መጽሐፍ ቅዱስ ሠይጣንን የሚውጠውን ፈልጎ "የሚዞር አንበሳ" ብሎ ይጠራዋል።

በዘመኑ ክርስቲያኖች ሠይጣንን አሳንሶ ማየት ፋሽን ሆኗል። እንደ ቀላል ነገር ሠይጣንን ችላ የማለትና በፌዝ የማለፍ አዝማሚያ አለ። አንዳንዶቹ እንዲያውም ህልውናውንም ይክዳሉ። ሆኖም በየዕለቱ በብልጠት ዘዴው ለጥቃት የሚጋለጡ ወንዶችና ሴቶች ባሉበት ማህበረሰብ ውስጥ የሠይጣንን ምህረት የለሽ ጥቃትና የማጥፋት ዘመቻውን እያየን ነው። በአካል ባናየውም ጭካኔ በተሞላ ጥቃቱ የሰዎች ህይወት ሲሰቃይና ሲጎሳቆል እንመለከታለን።

*ይህ ሁኔታ ካውጋር ከተባለ(ነብር የሚመስል) አውሬ ጋር ያጋጠመኝ የነበረውን ፍጥጫ ያስታውሰኛል። ብዙ ጊዜ ይህ ጮሌ ፍጥረት በሌሊት ወደ መንጎቼ መሀል ይገባና በመንጋው መሀል ከፍተኛ ሽብር ይፈጥራል። አንዳንድ ሴት በጎችን ተገድለው፣ ደማቸው ፈስሶ፣ ጉበታቸው ተበልቶ ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ተበጭቀውና በጥፍር ተቧጠው ይገኛሉ። በዚህ ሁኔታ ይህ ትልቅ ድመት መሳይ አውሬ ልክ ድመት ቤት ውስጥ አይጥ ባገኘች ጊዜ ሳትበላት በፊት እንደምትጫወትባት በበጎቹ መጫወት ይጀምራል። አንዳንዶቹ ጠጉራቸው በከፍተኛ ሁኔታ ይነቀላል። በእንዲህ ዓይነቱ ሁከት ውስጥ ከድንጋጤ የተነሳ አንዳንዶቹ በጎች ተደናቅፈው ወድቀው አጥንታቸው ይሰበራል ወይም በድንጋያማ ቦታ ላይ ወድቀው እግራቸውና ሌላው አካላቸው ይጎዳል።*

*ያም ሆኖ ግን ጉዳት፣ የሞቱ በጎች ፣ የቆሰሉ በጎች ቢኖሩም እና በመንጋው መካከል ከፍተኛ ስጋት ቢከሰትም አንድም ጊዜ ካውጋሩን በጋጣ ውስጥ አይቼው አላውቅም። የአውሬዎቹን ወረራ ለማወቅ እስከሚያስቸግር ድረስ ብልጠትና ብልሀት የተሞላበት ነበር።*

ሁልጊዜ ወደ ክርስቶስ ይበልጥ ቀረብ ብለን ብንጓዝ ያዋጣናል። ያ ደህንነት ያለበት ብቸኛ ሥፍራ ነው። ሁልጊዜ ባልታሰበ ጊዜ ለነጣቂ አውሬ የሚዳረጉት ከመንጋው ርቀው የሚጓዙ፣ አውደልዳይና ተቀበዝባዥ በጎች ናቸው። በአጠቃላይ እረኛው በበጎቹ የድረስልን ጩኸት ከመንቃቱ በፊት አጥቂዎቹ ያመልጣሉ። በእርግጥ አንዳንዶቹ በጎች ከጥቃቱ የተነሳ ፍርሃቱ አፋቸውን ስለሚለጉመው፣ ደማቸው መፍሰስ እስኪጀምር ድረስ ‹ባ› ማለት እንኳ አይችሉም።

በክርስቲያኖችም እንዲሁ ነው። ብዙዎቻችን ከአቅማችን በላይ በሆነ የጠለቀ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንገባለን፤ ለእርዳታ መጮህ እስከሚያቅተን በፍርሀት አንደበታችን ይዘጋል፤ እንዲያውም በአጠቃላይ በጠላታችን ጥቃት ሥር እንፍገመገማለን፡ ፡

# በጎች በዘይት መቀባት ለምን ያስፈልጋቸዋል?

" ...ራሴን በዘይት ቀባህ፤ ጽዋዬም የተረፈ ነው።"

መዝሙር 23፡5

ዘመናዊ የእረኝነት ጥበብም እንኳ የመቀባትን አስፈላጊነት ያስረዳል። የእረኛው የመቀቢያ ዘይት በጎቹን ለማሸት ይጠቀማል። የቅባት ዘይት ዝንቦችን ያባርራል ቁስልም ይፈውሳል። ዝንቦች የቤ/ክ አባላትን የሚያጠቁ ክፉ መናፍስትን የሚወክሉ ናቸው። ቁስሉ የሚከሰተው ሰዎች በዚህ ምድር ላይ ሲኖሩ ከሚገጥማቸው ሁናቴ ነው።

ህዝቡ ያለመቋረጥ ከሚያጠቁ ከሚክሱና ወደ ፈተና ከሚከቱ አጋንንቶች ነጻ ለመሆን እጅግ ይፈልጋሉ። ሰዎች መራራ ከሆነ ከዚህ ህይወት ቁስል መፈወስ ይፈልጋሉ።

ይህን በልባችን ሊያደርግ የሚችለው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ብቻ ነው። በሚያስገርም ሁኔታ ዘመናዊው እረኛ ከበጎች ላይ ተባዮችን ለማስወገድና ቁስላቸውን ለመጠገን ዘይት እንዴት በተግባር ጥቅም ላይ እንደሚውል ይገልጻል።

## 1. ዘይት ዝንቦችንና ሌሎች ነፍሳትን የሚያስወግደው እንዴት ነው?

በእረኞች ቋንቋ ‹‹የበጋ ወቅት የዝንቦች ወቅት ነው››። ይህን ሲሉ በሞቃት የአየር ሁኔታ ወቅት የሚፈሉትን የነፍሳት መንጋ ማለታቸው ነው። በበጋ ወቅት ዝንቦች እና ሌሎች ነፍሳት በእንስሳት ላይ የሚያስከትሉትን ከፍተኛ ችግሮች የሚያውቁት ከብት የሚያረቡ ሰዎች ወይም ስለ ዱር አራዊት ባህርይ ጥናት ያደረጉ ብቻ ናቸው።

ከብቶችን ከሚያውኩትና ህይወታቸውን ሲኦል ከሚያደርጉ ተባዮች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፦ እጬ በከብት ቆዳ ስር የሚፈለፈል ዝንብ፣ ፈረስና በግን የመሳሰሉትን

የሚያጠቃ ተባይ፣ የአፍንጫ ተባይ፣ የአጋዘን ተባይ፣ ጥቁር ተባይ፣ የወባ ትንኝ እና ሌሎች ባለ ትንንሽ ክንፍ ተባዮች ይገኙበታል። በበጋ ወቅት የሚፈለፈሉ እነዚህ ተባዮች በእንስሳት ላይ የሚፈጽሙት ጥቃት ወርቃማውን የበጋ ወራት ለበጎች  የስቃይ ዘመን እንዲሆንባቸው ከማድረጉም ሌላ ከሞላ ጎደል ወደ ጥፋት የሚገፋቸው ነው።

በጎች ብዙ ጊዜ የአፍንጫ ዝንብ የሚባለው ዝንብ በጣም ያስቸግራቸዋል። ዝ-ዝ-ዝ እያሉ በበጉ ራስ አካባቢ ይበሩና በበጎቹ አፍንጫ ውስጥ በሚገኘው ንፍጥ ላይ እንቁላላቸውን ለመጣል ሙከራ ያደርጋሉ። ከተሳካላቸው እንቁላሎቹ ተፈልፍለው ትንንሽ ቀጫጭንና ትል የሚመሳስል እጭ ይወጣል። ወዲያውም በአፍንጫ ውስጥ ለውስጥ ወደ በጉ ራስ መግባት ይጀምራሉ። ከዚያም ሥጋው ውስጥ በመግባት መጥፎ እባጭ በማስከተል በጎቹን ይረብሻሉ።

ከዚህ ሥቃይ ለመገላገል ሲሉ በጎቹ ሆን ብለው ግንባራቸውን ከዛፎች፣ ከአለት፣ ከምሰሶና ከጥሻ ጋር ያጋጫሉ። አፈር ውስጥ ያሹታል ደግሞም ያገኙትን እንጨት ሁሉ ይመታሉ። የተባዮቹ ጥቃት የከፋ በሚሆንበት ጊዜ በጎቹ ከሥቃያቸው ፋታ ለማግኘት ቅጥ ያጣ ሙከራ በሚያደርጉበት ጊዜ ሊሞቱ ይችላሉ። ብዙ ጊዜ በነዚህ ተባዮች የሚደርሰው ጥቃት ከፍ ያለ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ዐይነ ሥውርነት ያደርሳል።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የአፍንጫ ዝንቦች በአካባቢያቸው ድምጽ እያሰሙ በሚበሩበት ጊዜ በጎቹ በፍርሃት ይያዛሉ። ከእነዚህ አሰቃዮቻቸው ለማምለጥ ይወራጫሉ። መሬቱን በእግራቸው ይመታሉ። በግጦሽ ቦታው ላይ ወዲያና ወዲህ በመራወጥ በተቻላቸው መጠን ከዝንቦቹ ለማምለጥ ይጥራሉ። ሊያስጠልላቸው በሚችል ጥሻ ወይም ጫካ ውስጥ ይደበቃሉ። አንዳንዴ ግልጽ በሆነ ቦታ ለመጋጥ እምቢ የሚሉበት ጊዜ አለ።

‹‹የዝንቦች ወራት››ን አስቸጋሪ ሁኔታ መቋቋም የሚያስችለው እረኛው የበጎቹን ባህሪ ለመከታተል የሚሰጠው ትኩረት ነው። *መጀመሪያ ተባዮቹ ገና ብቅ ሲሉ በበጎቹ ራስ*

ላይ ፀረ ተባይ መድሃኒት ይረጯል። ከአፍንጫ ዝንብ እንዲጠበቁ የተልባ ዘይት፤ድኝ እና ሬንጅ ተቀላቅሎ በበጎቹ አፍንጫ ራስ ላይ ይቀባል።

ይህ ሕክምና በበጎች ዘንድ እንዴት አስገራሚ ለውጥ ያመጣ መሰላችሁ! ልክ ቅባቱ በበጎች ራስ ላይ ሲያርፍ በጎቹ ፈጣን የባህሪ ለውጥ ያሳያሉ። መበሳጨት፤ መደንበር፤ ሰላም ማጣትና መቅበጥበጥ ቀጥ ይላል። በዚያ ምትክ በጎቹ ረጋ ብለው መመገብ ይጀምራሉ፤ ከዚያም እርፍ ብለው ይተኛሉ።

ልክ እንደ በጎቹ ‹‹ዝንቦችን›› ከህይወቴ ለማስወገድ የማያቋርጥና በየጊዜው የሚታደስ ቅባት መቀባት ይኖርብኛል፤ የተለያየ ባሕሪ ካላቸው ሰዎች ጋር የሚገጥመንን የማያቋርጥ ግጭት ለመቋቋም ሁልጊዜ በቸሩ እግዚአብሔር መንፈስ መቀባት ያስፈልገናል።

በጎችን አንድ ጊዜ ብቻ ዘይት፤ ድኝ ሬንጅ መቀባት ለበጋው ወራት በሙሉ በቂ አይደለም፤ መደጋገም ያለበት ሂደት ነው፡፡ አዲስ ፀረ ተባይ ውጤታማ ይሆናል።

በህይወቴ እንደ ደስታ፤ እርካታ፤ ፍቅር፤ ትዕግስት፤ ራስን መግዛትና ሰላም ያሉ ባህርያት እንዲበዛ የሚያደርገው በየእለቱ በአእምሮዬ ላይ የሚፈሰው የሚከናወን የእግዚአብሔር ቸር መንፈስ ቅባት ነው። ይህ ደግሞ በየእለቱ በበርካታ የእግዚአብሔር ልጆች ባህሪ ላይ ከሚታየው ቁጣ፤ ተስፋ መቁረጥና ብስጭት ጋር ሲነጻጸር ሰፊ ልዩነት ይታያል።

## 2. በዘይት መቀባት ቁስልን የሚጠግነው እንዴት ነው?

የበጋ ወራት ለበጎች ‹‹የዝንቦች ወቅት›› ብቻ አይደለም። ‹‹የቆዳ በሽታ›› ወቅትም ነው። የበጎች የቆዳ በሽታ የሚቆጠቁጥና ከፍተኛ ተዛማች የሆነ በዓለም ዙሪያ ሁሉ የተለመደ በሽታ ነው። በዓይን ለማየት በማይቻል በሞቃት አየር አማካኝነት የሚመጣው ‹‹የበጎች የቆዳ በሽታ›› ከበሽተኛ በግ ወደ ጤነኛው በግ በንክኪ እየተላለፈ መንጋውን በሙሉ ያዳርሳል። ‹‹የበጎች የቆዳ በሽታ›› ብዙ ጊዜ የሚገኘው በራሶቻቸው አካባቢ ነው። በጎች ደስ በሚያሰኝና ለስለስ ባለ

ሁኔታ ራሳቸውን መታከክ ይወዳሉ። ሁለት በጎች በግምባሮቻቸው እርስ በእርስ በሚተሻሹበት ጊዜ በሽታው በቀላሉ ከአንዱ ወደሌላው ይተላለፋል።

*በብሉይ ኪዳን ዘመን ለመስዋዕት የሚቀርበው በግ ነቀፋ የሌለበት መሆን አለበት ተብሎ ሲታወጅ በጸሐፊዎቹ አዕምሮ በዋነኝነት ያለው ሃሳብ እራሶቻቸው ከቆዳ በሽታ ነጻ መሆን አለባቸው የሚል ነው። በቀጥተኛ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ‹‹የቆዳ በሽታ›› በሃጢአትና በክፋት መበከልን ያመለክታል።*

*እንዲህ ዝንቦቹ ሁሉ ብቸኛው ውጤታማ የዚህ በሽታ ማጥፊያ ዘዴ የተልባ ዘይት ድኝና በሽታውን ሊያስወግዱ የሚችሉ ኬሚካሎችን መቀባት (መርጨት) ነው። በፓለስታይን አገር ጥንታዊ የዚህ በሽታ ማጥፊያ መድሃኒት ከድኝና ከቅመማ ቅመም ጋር የተቀላቀለ የወይራ ዘይት ነበር፡*

የበጎች እርባታ ባለባቸው ብዙ አገሮች እንደ ገንዳ ነገር ይሠራና በጎቹ በዚያ ውስጥ እንዲያልፉ ይደረጋል። እያንዳንዱ በግ ሰውነቱ ሁሉ እስኪሸፈን ድረስ በገንዳ ውስጥ ባለው መድሃኒት ውስጥ ይነከራል። በዚህ ጊዜ ለመዝፈቅ በጣም አስቸጋሪው የበጎቹ የሰውነት ክፍል ቢኖር ጭንቅላታቸው ነው። ስለሆነም በጭንቅላት አካባቢ ሊከሰት የሚችለውን የቆዳ በሽታ ለመቆጣጠር ጭንቅላታቸውን ደጋግሞ ወደታች መግፋት የግድ ያስፈልጋል። አንዳንድ እረኞች ይህን ለማድረግ ከሚወስዱት ጥንቃቄ የተነሳ እጆቻቸውን ይጠቀማሉ።

## ምዕራፍ 12

# የእረኛው ፅዋ የተረፈ መሆን ለበጎች ያለው ፋይዳ ምንድነው ?

"... በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።"

መዝሙር 23፡5

የውሃና የአረቄ ቅልቅል ያለበት ጠርሙስ የያዘ እረኛ እስካየሁበት ቀን ድረስ አንድ እረኛ በመዝሙሩ የተጠቀሰውን አይነት ፅዋ እንዳለው አላውቅም ነበር። ይህ የውሃና የአረቄ ቅልቅል በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ወቅት በብርድ የተቆራመዱ በጎች የፈውስ በረከትና ተሃድሶ ሆኖ ይፈሳል። የእረኛው ሞልቶ የተረፈ ፅዋ ለበጎቹ ህይወት ሰጪ ፅዋ ነው።

በእርግጥም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለዓለም ሁሉ ደሕንነትንና ፈውስን ሊሰጥ ፈሰሰ። የእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ፅዋ ለተቸገሩ በጎች ህይወትና ፈውስ ለማምጣት ሞልቶ ማፍሰስ አለበት። ልምድ ያለው እረኛ ፊሊፕ ኬለር ‹‹ሞልቶ በተረፈው ፅዋው›› በጎቹን እንዴት ያገለግልበት እንደነበር ይናገራል።

እንዲህ ይላል፤

> አውሎ ነፋስ ሊነሳ ይችላል ወይም ከፍተኛ ማዕበል ኮረብቶችን ሊሸፍን ይችላል። እረኛውና መንጋው አሰቃቂ በሆነ መከራ ውስጥ ሊያልፉ ይችላሉ።
>
> እዚህ ላይ ነው ‹‹ሞልቶ የተረፈው ፅዋ›› ትርጉም ሌላኛውን ገጽታ የተገነዘብኩት። በእያንዳንዱ ህይወት የመከራ ፅዋ አለ። ኢየሱስ ክርስቶስ በጌቴሴማኒ በጎልጎታ የተጨነቀውን ጭንቀት እንደ ፅዋው ወስዶታል። ስለሆነም ለሰው ልጆች ህይወቱን ባያፈስ ኖሮ እኛ በጠፋን ነበር።
>
> በጎቼን በምጠብቅበት ጊዜ የውሃና የአረቄ ቅልቅል የያዘ ጠርሙስ በኪሴ እይዛለሁ። እናት በግ ወይም ግልገሏ እርጥበት ላለው

ወይም ቀዝቀዛ የአየር ሁኔታ ተጋልጠው በቅዝቃዜ በሚቆራመዱበት ጊዜ በጉሮሯቸው ጥቂት ማንኪያ ያህል አንቆረቁርላቸዋለሁ። በብርድ ተቆራምደው የነበሩ በጎች በደቂቃ ውስጥ በታደሰ ኃይል በእግራቸው ቀጥ ብለው ይቆማሉ። በተለይ ግልገሎች ከአረቄ የተገኘው ሙቀት በሰውነታቸው ውስጥ በሚደርስበት ወቅት ጭራቸውን በደስታ ሲያወዛውዙ ማየት በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው።

ዋናው አስፈላጊ ነገር በብርድ የተቆራመደው በግ ወደ ከፋ ደረጃ ሳይደርስ በሰዓቱ መገኘቴ ነው። በማዕበል ውስጥ አብሬያቸው ሆኜ በስቃይ ውስጥ ያሉትን በንቃት መከታተል ነበረብኝ። በጎች በማስማራበት ወቅት ያጋጠሙኝ በግልጥ የማስታውሳቸው ገጠመኞች የሚያጠነጥኑት እኔና መንጋዬ ባለፍንባቸው አስከፊ ማዕበሎች ዙሪያ ነው።

የጠቆረ የባህር ሞገድ ደመና ከባህር ወደ ዳርቻ ሲስገመገም አያለሁ፤ ውሽንፍርና በረዶ ኮረብቶችን ሲከድን አያለሁ፤ በጎቼ መጠለያ ፍለጋ ወደ ረጃጅም ዛፎች ሥር ሲሯሯጡ አያለሁ፤ ከዚያም በውሃ የራሱ በብርድ የተቆራመዱና ቅስስ ያሉ በጎቼ ይታዩኛል። በተለይ ግልገሎቼ ሙሉ በሙሉ ያደገ ፀጉር ስለሌላቸው ስቃያቸው ይከፋል። አንዳንዶቹ ይረቱና መሬት ላይ ይተኛሉ፤ ይሕም ይበልጥ በብርድ ያቆራምዳቸዋል። በዚህ ጊዜ ነው የውሃና የአረቄ ቅልቅሉ የሚታደጋቸው። በተመሳሳይ መልኩ የፓለስታይን እረኞችም በቆፈን ለተያዙና በብርድ ለተቆራመዱ በጎቻቸው ከሚይዙት ወይን ለበጎቻቸው እንደሚያካፍሏቸው እርግጠኛ ነኝ።

ይሕም ከተቀበለው መከራ የተነሳ የፈሰሰው ይህ እውነተኛ ደሙ የሆነውን ወይን ሞልቶ ከተረፈው ፅዋው በጎልጎታ ለኔ ያፈሰሰው አስገራሚ የጌታዬ ምሳሌ ነው። በየትኛውም ማዕበል ውስጥ ሁልጊዜ ከኔ ጋር ነው። እረኛዬ ህዝቡን ለማስፈራራት የሚቀርቡትን እያንዳንዱን መከራ በንቃት የሚከታተል እረኛ ነው። እርሱ ከእኛ ቀድሞ በመከራ ማዕበሎች ውስጥ አልፏል፤ ሸክማችንን ተሸከመ፤ ሐዘናችንንም ተካፈለ።

## ምዕራፍ 13

# በጎች በእረኛቸው ቤት መኖር የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?

"... በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።"

መዝሙር. 23:6

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ መኖር ማለት በየትም ሥፍራ በሀያው ጌታ እንክብካቤ ውስጥ መኖር ማለት ነው። በተራራ ይሁን በሸለቆ በጠባቂያችን ጥበቃ ሥር እስካለን ድረስ በጌታ ቤት ውስጥ ነን። ስለነሱ በሚገደው እረኛ ጥበቃ ሥር ባሉ በጎችና በክፉና ግድ በሌለው ጥበቃ ሥር ባሉ በጎች መካከል ልዩነት አለ። ፊሊፕ ኬለር ክልምዱ በመነሳት በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ ማሳያ ይሰጣል።

ይሕንን የመዝሙር 23 የመጨረሻ ክፍል ባሰላሰልኩ ቁጥር በመጀመሪያው የበጎች ጋጣዬ ውስጥ የተከሰቱ ትዝታዎች ግልጥ ብለው በውስጤ ይመጣሉ።

የክረምቱ ወራት ከቀዝቃዛ ዝናብና ብርዱ ጋር በሚመጣበት ጊዜ የጎረቤቴ ሀመምተኛ በጎች ላታቸውን ወደ ውሸንፍሩ አድርገው የኔ በጎች በደስታ ወደተሰማሩበት ያማረ ሜዳ እየተመለከቱ አጥሩ ጋር ስብስብ ብለው ይቆማሉ።*(እነዚያ አዕምሮ በጎደለው እረኛ ሥር ያሉ ምስኪን ያለ አግባብ የተያዙና የተረሱ በጎች የአመቱን አብዛኛውን ክፍል ከሥቃይ በስተቀር የሚያውቁት ነገር የለም። በጋውን በሙሉ በጠኔ ይሰቃያሉ። ቀጫጭኖችና በተለያዩ በሽታዎች፤ በቆዳ በሽታና በጥገኛ ህዋሳት የተጠቁ ናቸው። በዝንቦች በመሰቃየታቸውና በአውሬ በመጠቃታቸው ምክንያት አንዳንዶቹ ቀጫጭን እግሮቻቸው የመነመነውን ሰውነታቸውን መሸከም እስከማይችል ድረስ የከሱና የደከሙ ናቸው።)*

በአይኖቻቸው ላይ አንድ ቀን አጥር ሰብረው ወይም በቀዳዳ ሾልከው ራሳቸውን ነፃ ማድረግ እንደሚችሉ ተስፋ የማድረግ ጭላንጭል ይታያል። አልፎ አልፎ ይህ ክስተት በተለይ በገና

አካባቢ ይፈጠራል። ይህ ወቅት የባህሩ ውሃ ከአጥሩ በላይ ከፍ እያለ ዝቅ የሚልበት ወቅት ነው። እነዚያ የመነመኑ እርካታ ያጡና የተራቡ በጎች ይህን አጋጣሚ ይጠባበቃሉ። የባህሩ ውሃ እንደዚህ ከፍ በሚልበት ጊዜ ዕድላቸውን በመጠቀም በአጥሩ ጥግ አካባቢ ከፍ ባለው ውሃ አማካኝነት ተንሸራትተው ወደኛ አረንጓዴ የሣር ግጦሽ ሾልከው ይገባሉ።

ሁኔታቸው እጅግ አሳዛኝ ነው። ባልለመዱት ሁኔታ ያገኙትን መልካም ሣር በገፍ በሚበሉበት ጊዜ ጉዳት ይደርስባቸዋል። ጨጓራቸው ምግብ መፍጨት ያቆማል። ይህም አንዳንድ ጊዜ ለሞት ሊዳርጋቸው ይችላል። በአንድ ዝናባማ ቀን ሶስት የጎረቤቱ ወላድ በጎች ከአጥሩ አጠገብ በሚገኝ ዛፍ ሥር ተስፋ በሌለው ሁኔታ ተኝተው እንዳየኋቸው በግልጽ አስታውሳለሁ። ሶስት ያረጁ፣ የተበላሹና የሻገቱ ጆንያዎች ተቆልለው ይመስላሉ። አጥንታም የሆነ እግራቸውም ሊሸከማቸው የማይችልበት ደረጃ ላይ ነበር።

*በጋሪ ላይ ጫንኳቸውና አዕምሮ ወደ ጎደለው ባለቤታቸው መለስኳቸው። በቀላሉ የሰላ ቢላ አወጣና የሶስቱንም ጉሮሮ በጠሰው። ትንሽ እንኳን ግድ አልሰጠውም። ይህ ብዙዎችን የሚገዛው የሰይጣን ትክክለኛ ምሳሌ ነው።*

ወዲያውኑ ኢየሱስ ስለራሱ በጎች ወደ አቅፉ የሚገቡበት የበጎች በር እንደሆነ የገለጸበት ሥዕል ወደ አዕምሮዬ መጣ። እነኚያ ምስኪን በጎች ወደኔ ጋጣ የመጡት በትክክለኛው በር አልነበረም። የእኔ አልሆኑም ነበር፤ በእኔ ባለቤትነት ወይም ጥበቃ ሥር አልገቡም። ይህ ቢሆን ኖሮ ያን ያህል መከራ አይደርስባቸውም ነበር።

ከክርስቶስ ርቀው ያሉት የሚገጥማቸው ይኸው ነው። አሮጌው ዓለም ክፉ ጋጣ ነው፤ ባለቤቱም ጨካኝ ሰይጣን ነው። ስለሰዎች ነፍስም ሆነ ደህንነት ቅንጣት ያህል ግድ የለውም። በጨካኝ አገዛዝ ሥር ያሉ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት ለመግባት የሚናፍቁ አሉ፤ መልካም እንክብካቤውንና ጥበቃውን የሚጠሙ የተራቡና እርካታ ያጡ ብዙዎች አሉ።

## ምዕራፍ 14

# ያለ እረኛ መሆን ለበጎች ምን ትርጉም አለው?

1. ዓላማ ቢስነት፦ ሰዎች የሚያዋጣቸውና የሚያገባቸው እረኛ ከሌላቸው አላማቢሶችና የሚሄዱበትን አቅጣጫ የማያውቁ ናቸዉ።

ሙሴም እግዚአብሔርን እንዲህ ብሎ ተናገረው። "የእግዚአብሔር ማኅበር እረኛ እንደሌለው መንጋ እንዳይሆን፥ በፊታቸው የሚወጣውን በፊታቸውም የሚገባውን የሚያስወጣቸውንም የሚያስገባቸውንም ሰው የሥጋ ሁሉ መንፈስ አምላክ እግዚአብሔር በማኅበሩ ላይ ይሹመው።"

ዘኍልቍ 27፡15-17

2. መከፋፈል፦ እረኛ በሌለበት ሰዎች ይከፋፈላሉ ቤተሰብ አልባም ይሆናሉ።

"እርሱም፦ እስራኤል ሁሉ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች በተራሮች ላይ ተበትነው አየሁ እግዚአብሔርም፦ ለእነዚህ ጌታ የላቸውም እያንዳንዱም በሰላም ወደ ቤቱ ይመለስ አለ ብሎ ተናገረ።"

1ኛ ነገሥት 22፡17

3. ድካምና በሽታ፦ ያለእረኛ ሰዎች በበሽታ ይጠቃሉ፤ ዓቅመ ቢስ ይሆናሉ።

"የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቍናም ገዛችኋቸው። እረኛንም በማጣት ተበተኑ፥ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፥ ተበተኑም። በጎቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዘበዘዋል፥ በጎቼም በምድር ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል የሚሻም የሚፈልግም አልነበረም።"

ሕዝቅኤል 34፡4-6

4. መፍትሔ የሌለው ችግር፦ ያለ እረኛ የሆኑ ሰዎች ብዙ ያልተፈቱ ችግሮች ያሏቸው ናቸው።

"ተራፊም ከንቱነትን ተናግረዋልና፥ ምዋርተኞችም ውሸትን አይተዋልና ሕልምንም የሚያዩ በሐሰት ተናግረዋል፥ በከንቱም ያጽናናሉ ስለዚህም የባቸውምና እንደ በጎች ተቅበዝብዘዋል ተጨንቀውማል።"

ዘካርያስ 10፡2

## 5. በወጣቶች ላይ ጥፋት፦ በእረኛ እጦት በአመዛኙ የሚጎዱት ህጻናትና ወጣቶች ናቸው።

"ሰይፍ ሆይ፥ ባልንጀራዬ በሆነው ሰው በእረኛዬ ላይ ንቃ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እረኛውን ምታ፥ በጎቹም ይበተናሉ እጄንም በታናናሾች ላይ እመልሳለሁ።"

ዘካርያስ 13፡7

## 6. እጦትና እጥረት፦ እረኛ በሌለበት ሰዎች ፍላጎታቸው አይሟላም።

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።"

መዝሙር 23፡1

## 7. ከመስመር መውጣት፦ በጎች ለሕይወታቸው በብልጽግናና በበረከት ጎዳና ላይ ለመጽናት ምሪት ያስፈልጋቸዋል። በጎች ለህይወታቸው ብዙ ምሪቶችን ከእረኛው ይቀበላሉ።

"በሙሴና በአሮን እጅ ሕዝብህን እንደ በጎች መራሃቸው።"

መዝሙር 77፡20

"ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ፥ የእስራኤል ጠባቂ ሆይ፥ አድምጥ በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ፥ ተገለጥ።"

መዝሙር 80፡1

## ምዕራፍ 15

# እረኞችንም የሚያጠቃ የበጎች በሽታ

በየትኛውም ለውጤት የሚደረግ ጥረት ውስጥ በሥራ ላይ የሚያጋጥም አደጋ አለ። በሆስፒታሎች ሐኪሞች ብዙ ጊዜ የታካሚዎቻቸው በሽታ ይጋባባቸዋል። አንዳንዴ ሐኪሙ ከታካሚው በተጋባበት በሽታ ሊሞትም ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ ብዙ እረኞች በበጎች በሽታ ይጠቃሉ። አልፎ አልፎ እረኞቹ ከበጎቹ በከፋ ሁኔታ በበጎች በሽታ ይሰቃያሉ።

ይህ የሚሆንበት ምክንያት ‹‹እረኞቹ›› ‹‹በጎችም›› ስለሆኑ ነው። መጋቢ ‹‹እረኞች›› ሁሉ በእረኞች አለቃ በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነትና አመራር ሥር ናቸው። እረኞችን በጎችም የሚያደርጋቸው ይሕ ነው።

እረኞችና መጋቢዎች ብዙ ጊዜ በሌሎች አገልጋዮች ሥር ይሆናሉ። እነርሱም መታዘዝና መከተል ስለሚጠበቅባቸው በበጎች የሚደርሰው መከራ ሁሉ ይደርስባቸዋል።ቀደም ብዬ እንዳልኩት እረኞች ከበጎች ይልቅ የከፋ ‹‹የበጎች በሽታ›› ያጠቃቸዋል።

## ሰባት እረኞችን የሚያጠቁ የበግ በሽታዎች

### 1. መታከት

"ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።"

ማቴዎስ 9:36

መታከት ከበጎች በሽታ አንዱ ነው። መታከት በተመሳሳይ መልኩ የእረኞችም በሽታ ነው። ከሠይጣን ዘዴዎች አንዱ ክርስቲያኖች እንዲታክቱ፣ እንዲዝሉ ማድረግ ነው። "በልዑሉም ላይ ቃልን ይናገራል፥ የልዑልንም ቅዱሳን ይሰባብራል፥ ዘመናትንና ሕግን ይለውጥ ዘንድ ያስባል እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም በእጁ ይሰጣሉ።" (ዳንኤል 7:25)።

## 2. ዓላማ ቢስነት

ዓላማ ቢስነት ያለእረኛ የሆነ በግ በሽታ ነው። እረኞችም የእረኞችን አለቃ ምሪት የማይከተሉ ከሆነ ዓላማ ቢሶች ሊሆኑ ይችላሉ። በርካታ መጋቢዎች ዐይናቸውን ከታላቁ እረኛ ላይ አንስተው የሰዎችን ሃሳብ መከተል ይጀምራሉ። ለዚህ ነው መጋቢዎችን በፖለቲካ፣ በንግድ፣ በማህበራዊ አገልግሎቶችና በሌሎች ሰዎችን ሊያስደስት በሚችሉ ሥራዎች ውስጥ ገብተው የምታገኟቸው ለእረኛውም የጌታን ድምጽ መከተል እጅግ አስፈላጊ ነው። ከዓላማ ቢስነት ነፃ ያውጣህ!

«ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።»

ማቴዎስ. 9፡36

«ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል ሕግን የሚጠብቅ ግን የተመሰገነ ነው።»

ምሣሌ 29፡ 18

## 3. መጠውለግ

«ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።»

ማቴዎስ 9፡36

ብዙ በጎች ጠውልገዋል፣ መራመድም አቅቷቸዋል። አንዳንዶ ወይ በሽክም መሄድ አለባቸው አሊያም መታረድ አለባቸው። በኛ አውድ መጠውለግ የሚከሰተው እረኛው አገልግሎቱን ሲተው ነው። ጠወለገ ስንል አገልግሎቱን አቆመ ማለታችን ነው።

በጎች የሚጠወልጉት እረኛ ሲያጡ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጎታል። የጌታን ፊት መፈለግ ስለሚያበረታታህ ከመጠውለግ ትድናለህ። የእረኛህ በአጠገብህ መሆንና የሚያሳድርብህ ተጽዕኖ ከመጠውለግ የሚጠብቅህ አንዱ መንገድ ነው።

## 4. መበታተን

«ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።»

ማቴዎስ. 9፡36

ብዙ በጎች እረኞች ስለሌላቸው ተበታትነዋል፡፡ በዚያው መልኩ እረኞችም ተበታትነው የየትኛውም ህብረት ወይም ቤተሰብ አባል አይደሉም፡፡ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ የምታዳምጥ ከሆነ በእርግጠኝነት የአንድ ሰፋ ያለ ህብረት አባል እንድትሆን ይናገርሃል፡፡ በራስህ የምትንቀሳቀስ አገልጋይ ብትሆንም እንኳ የአንድ ቡድን ወይም ህብረት አካል ብትሆን እጅግ ትጠቀማለህ፡፡ በአገልግሎት ዘመኔ ታላላቅ በረከቶችን የምካፈለው ከሌሎች መንፈሳዊ ህብረቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ስለማደርግ ነው፡፡

## 5. ጭንቀት

«ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።»

ማቴዎስ. 9፡36

ብዙ ዓይነት አስጨናቂ ሁኔታዎች ወደ እግዚአብሔር አገልጋይ ይመጣሉ፡፡ መጋቢ መሆንህ ከዚህ እውነታ ውጪ አያደርግህም፡፡ ነገር ግን በህይወትህ እረኛ ካለህ በአገልግሎትህ በሚገጥምህ ሥቃይ ውስጥ እንድታልፍ በእርግጠኝነት ይረዳሃል፡፡ ዳዊት ብዙ ጊዜ ተጨንቋል፡፡ በጠላቶቹ የተከበበባቸው ጊዜያቶች ነበሩ፡፡ ብዙ ጊዜ ለክፉ አደጋ ተጋልጧል፡፡

እንዲህ ብሎ ጮኸ፡-

"መከበቡንስ ከበቡኝ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው፤ ንብ ማርን እንዲከብብ ከበቡኝ፥ እሳትም በእሾህ ውስጥ እንዲነድድ ነደዱ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው።"

መዝሙር. 118፡11-12

ነገር ግን በጨነቀው ጊዜ ወደ እረኛው ጮኸ፡፡ እግዚአብሔር እረኛው ነበር እግዚአብሔርም ረዳው፡፡

‹‹በተጨነቅሁ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት ሰማኝ አሰፋልኝም። እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፥ አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?»

መዝሙር 118፡ 5-6

## 6. ግራ መጋባት

ዐበአገልግሎትህ እያደግህ ስትመጣ ግራ መጋባት ከአስፈሪ ጠላቶችህ አንዱ ይሆናል። በግራ መጋባት ወቅት ‹‹ይህ ትክክል ነው ወይስ አይደለም?›› የሚል ጥያቄ ትጠይቃለህ። በግራ መጋባት መንፈስ ስትጠቃ ግልጥ ካልሆነ ጉዳይ ጋር ትንቅንቅ ውስጥ ትገባለህ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ከተጻፉ ጉዳዮች ጋር መታገል ትጀምራለህ። ስለራስህ እርግጠኛ ስለማትሆን ጉዞህን ለመቀጠል ታላቅ እምነት ያስፈልግሃል። የሚመሩበት መጽሀፍ ቅዱስ ስላልነበራቸው እግዚአብሔር እንደተናገራቸው ባመኑበት መንገድ ይጓዙ እንደነበሩት የቀደሙት አባቶች ትሆናለህ።

በእርግጥም በእንዲህ ያለው ወቅት የሚያረጋጋህና የሚያስረግጥልህ የእረኛህ ምሪት ነው። የምለውን መረዳት የምትችለው ወደዚያ ደረጃ ስትደርስ ብቻ ነው።

> «ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።»
>
> ማቴዎስ 9፡36

ግራ መጋባትህን ያራዘመው ከእረኛህ መለየትህ ነው። እስራኤላዊያን በበደላቸው ምክንያት ከጌታ በመለየታቸው ጸኑ። ይህም የበለጠ ግራ መጋባትን ፈጠረባቸው።

> «ጌታ ሆይ፥ ጽድቅ ለአንተ ነው እንደ ዛሬም ለእኛ ለይሁዳ ሰዎችና በኢየሩሳሌም ለሚቀመጡ ለእስራኤልም ሁሉ በቅርብና በሩቅም ላሉት አንተን በበደሉበት በበደላቸው ምክንያት በበተንህበት አገር ሁሉ የፊት እፍረት ነው።
>
> ጌታ ሆይ፥ በአንተ ላይ ኃጢአት ስለ ሠራን ለእኛና ለነገሥታቶቻችን ለአለቆቻችንና ለአባቶቻችንም የፊት እፍረት ነው።»
>
> ዳንኤል 9፡7-8

ወደ ጌታ ተጠጋ ደግሞም ወደ እረኛህ ተጠጋ። ይህም በአገልግሎትህ ካለ ግራ መጋባት ነፃ ያወጣሀል። አንድ ቀን ዛሬ አንተን የገጠመህን ችግር እርሱ እንዴት እንዳሸነፈው ይገልጽልሀል። አንተ ዛሬ የገጠመህ ችግር በአንድ ወቅት እረኛህም አጋጥሞት እንደነበረ ስትረዳ ትበረታታለህ። ዛሬ እንዴት ልታሸንፍ እንደምትችል ይበራልሃል፤ ጥበብንም ታገኛለህ።

# ምዕራፍ 16

# በጎች ለምን ይታመማሉ?

## 1. በጎች የእረኛቸውን ጌትነት (ባለቤትነት) ካልተቀበሉ ይታመማሉ::

‹‹እግዚአብሔር እረኛዬ ነው›› የሚለው ዐረፍተ ነገር እረኛ የበጎች ባለቤት መሆኑን የሚያስረዳ ጥልቅ መገለጥ ነው:: የእረኛው ጌትነት እረኛው በበጎቹ ላይ ያለውን ፍጹም ባለቤትነት ያሳያል:: በዚህ ከፍተኛ የባለቤትነት መብት በጎቹን ሊመራ፣ አቅጣጫ ሊያሳይና ተሀድሶ ሊያደርግላቸው ይችላል:: የራሱ ንብረቶች ስለሆኑ ብዙ ጥቅሞችን ወደ በጎቹ ያመጣል::

በየትኛውም ግብርና ወይም አገር እያንዳንዱ በግ ወይም ላም የራሱ ባለቤት እንዳለው ግልጽ ነው:: ያ ሰው የበጉ ባለቤትም፣ ዋና እረኛም ነው::

> "እግዚአብሔር በእኔ ላይ ባለንብረት እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።
> በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።
> ነፍሴን መለሳት፤ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ (አቅጣጫን አሳየኝ)።
> በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ፣ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን (ተስፋ መቁረጥን) አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።
> በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ፤ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ(የተትረፈረፈ አቅራቦት) ነው።
> ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።"

መዝሙር 23

የሚያሳዝነው፣ አንዳንድ በጎች በህይወታቸው የእረኛውን ጌትነት አይቀበሉም:: ይህም አቋማቸው ከእረኛቸው ኃይልና ፍቅር ውጭ ያደርጋቸዋል:: ከብርቱ ጠባቂያቸው ራሳቸውን ለይተው ባለማወቅ ራሳቸውን ይጎዳሉ:: በአገልግሎት ውስጥ ከእረኛቸው ጋር ያላቸውን ቁርኝት የሚያቋርጡ አገልጋዮች በቀላሉ ይደርቃሉ፣ ቀስ በቀስም ይጠፋሉ::

## አንድ በግ የእረኛውን ጌትነት አለመቀበሉ የሚታወቅባቸው ምልክቶች

ሀ. የመጋቢያቸውን ስብከት የማይሰሙ በጎች ትዕዛዝ የማያከብሩ የእረኛቸውን ጌትነት የማይቀበሉ በጎች ናቸው።

ለ. በመጋቢያቸው የተፃፉ መፃህፍትን የማያነቡ የእረኛቸውን ጌትነት ያልተቀበሉ በጎች ናቸው። ከመፃህፍቱ የሚገኘውን በረከት መካፈል ያቆማሉ። ሁሉን አዋቂ ነን ስለሚሉ ለእረኛቸው አይገዙም።

ሐ በገላትያ 6:6 መሠረት መጋቢያቸውን የማያከብሩ በጎች የእረኛቸውን ጌትነት ያልተቀበሉ ናቸው። እንደ መሪያቸውና አስተማሪያቸው ያልተቀበሉትን ምን ይሁን ብለው ያክብሩ?

መ. በጎች ጠቃሚ የሆኑ ፕሮግራሞችን ባለመካፈል ከእረኛቸው አገዛዝ ነፃ መሆናቸውን ያውጃሉ። ፕሮግራሞችን አለመካፈል መጋቢውን ‹‹ እኔም ከአንተ አላንስም ስለዚህ ወዳንተ ፕሮግራም መምጣት አያስፈልገኝም›› ብሎ እንደመናገር ነው።

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም። መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም።»

ዮሐንስ 13:16

## 2. በጎች ከእረኛቸው ስር ካልተመገቡ ይታመማሉ። እረኞች ደግሞ ከእረኞች አለቃ ካልተቀበሉ ይታመማሉ።

«የዮሐንስ ልጅ ስምዖን ሆይ! እነዚህ ከሚወዱኝ ይበልጥ ትወደኛለህን? አለው።» እርሱም « አዎ ጌታ ሆይ! እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ» ሲል መለሰለት። ኢየሱስም «ግልገሎቼን መግብ» አለው።

ዮሐንስ 21:15-16

## 3. በጎች ጥበብንና እውቀትን ባለማቋረጥ ከእረኛቸው ካልተቀበሉ ይታመማሉ።

«እንደ ልቤም በግ ጠባቂችን እሰጣችኋለሁ፥ በእውቀትና በማስተዋልም ይጠብቁአችኋል።»

ኤርምያስ 3:15

## 4. በጎች የራሳቸውን እረኛ የማይከተሉ ከሆነ ይታመማሉ:: እንዲህ ያሉ ሰዎች አንድ ሺህ የተለያዩ ሰዎችን ይከተላሉ እንጂ የሚከተሉት የራሣቸው የሆነ እረኛ የላቸውም::

«እንደምወዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልገሥጻችሁ እንጂ ላሳፍራችሁ ይህን አልጽፍም።

በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የሉአችሁም እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጃችኋለሁና።

እንግዲህ እኔን የምትመስሉ (የምትከተሉ) ሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ።»

1ኛ ቆሮንቶስ 4፡1-16